# የመጠሪያ ስሞች

## መዝገብ

የመጠሪያ ፣ የክርስትና እና የማዕርግ ስሞችን
ያካተተ በታሪክ ላይ የተመሠረተ ።

ዋና ጠቀሜታው ወላጆች ለሕፃናት ልጆቻቸው
ስም ለመስየም ምርጫ እንዲያገኙ ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

ጥቅምት ፳፩ ቀን ፪፻፩ ዓ. ም.
October 2008
ከ 6000ሺ በላይ ስሞችን የያዘ።
የመጀመሪያ እትም

ለ ____________________

ከ ____________________

ቀን ____________________

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

© 2008 By Melak Berhan BERHANU BISRAT
All Rights Reserved

የመጀመሪያ እትም

ኤች. ዋይ ኢንተርናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት
H.Y. International Printers Enterprise Pvt.Ltd.Co
P.O Box 50676
Addis Ababa

ስለጽሑፉ አስተያየት ቢኖርዎ
በዚህ አድራሻ መገናኘት ይቻላል።
P.O.Box 24842 Code 1000
Addis Ababa





ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በመላው አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ
የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የበላይ ጠባቂ ለነበሩት
እና
በስማቸው ለተሰየመው
"አቡነ ዮሐንስ የልጆች ትምህርት ቤት"
መታሰቢያ ይኹንልኝ።



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በመላው አውሮፓ ሊቀ ጳጳስ
የርእሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም
የበላይ ጠባቂ ለነበሩት
እና
በስማቸው ለተሰየመው
"አቡነ ዮሐንስ የልጆች ትምህርት ቤት"
መታሰቢያ ይኹንልኝ።

# ምስጋና

*መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት (ምሳ. 12:4)* እንደተባለው በሥራዬ ረዳት ሸና ላበረታታችኝ ባለቤቴ መቅደሰወርቅ ዓለሙ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ በማንበብ ሐሳባቸውን ላካፈሉኝ ኢንጂነር ከበደ ኀበና፣ ዶክተር ማንደፍሮ በላይነህ፣ ልጅ ወሌ ነጋ እና የመጽሐፉን ሽፋን ንድፍ ላዘጋጁልኝ ለአርክቴክት አበባው መስፍን ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

ይህ መጽሐፍ ለኅትመት በቅቶ አንባብያን እጅ እንዲደርስ የተባበሩኝ አቶ ታምራት ከበደ እንዲሁም የተራዱኝን እማሆይ ትርሢት እኅለን በእግዚአብሔር ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

የድካም ዋጋ ውጡቱ እንዲታይ በማተሚያ ድርጅታቸው ለኅትመት እንዲበቃ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉልኝን፣ ኤች ዋይ ኢንተረናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት ኃላፊ አቶ ሀብቴ ፊርሻ እና ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ይሳለሙሽ ተክሌ በተጨማሪም የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞ ስለትብብራቸው በእግዚአብሔር ስም ከልብ አመሰግናለሁ::



# ማውጫ


መቅድም ........................ ገጽ

ምዕራፍ ፩

መጠሪያ ስሞች (ስመ ተጸውዖ) ........ 10
- (ሀ) ወላጆች የሚሰይሙት ስም ........ 10
- (ለ) ስምን መልአክ ያወጣዋል። ........ 13
  - (፩) ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ........ 13
  - (፪) እቴጌ መሶበወርቅ ........ 14
  - (፫) ቅዱስ ላሊበላ ........ 15
  - (፬) ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ ........ 16
- (ሐ) የባሕርይ ስም (ስመ ባሕርይ) ........ 16
- (መ) የመጠሪያ ስም በቅኔ ምርምር ........ 17
- (ሠ) የፍቅርና የቍልምጫ ስሞች ........ 20
- (ረ) ለቤተሰብ የሚሰጥ ያክብሮት ስም ........ 22
- (ሰ) በጥንታዊው ትምህርት ቤት የሚሰየም ስም ........ 23
- (ሸ) የተዋሐዱ የመጠሪያ ስሞች ........ 24
  - (፩) የወንድ የመጠሪያ ስም ........ 26
  - (፪) የቤት የመጠሪያ ስም ........ 122

## ምዕራፍ ፱


የክርስትና ስሞች (ስመ ጥምቀት) ........................ 196

(ሀ) የሚያከራክሩ የክርስትና ስሞች ........................ 197

(ለ) የክርስትና አባትና እናት ........................ 199

(ሐ) የወንዶች የክርስትና ስሞች ........................ 201

(መ) የሴቶች የክርስትና ስሞች ........................ 220


## ምዕራፍ ፲


የማዕረግ ስሞች (ስመ ተቀብዖ) ........................ 232

(ሀ) ጳጳሳት ቅብዐ ክህነት ሲቀቡ የሚሰየሙት ስሞች........ 232

(ለ) የሥልጣነ ክህነትና ያስተዳደር የማዕርግ ስሞች ........ 234

(፩) በደብር አለቆች የማዕርግ ስም ........ 234

(፪) በደብር አገልግሎት የማዕርግ ስሞች ........ 234

(፫) የአብነት ት.ቤት መምህራን የማዕርግ ስሞች... 235

(፬) የሊቅነት፣ የመዘምርነት የማዕርግ ስሞች ...... 235

(፭) የመነኩሳት፣ የገዳማውያን የማዕርግ ስሞች .. 236

(ሐ) ነገሥታት ቅብዐ መንግሥት ሲቀቡ የሚሰየሙ ስሞች... 236

(፩) አባ የሚለው የማዕርግና የመጠሪያ ስም........ 239

(፪) ንገሥታት ማዕረግ ሲሰጡ የሚሰየም ስም........ 241

(፫) ማንኛውም ሰው የሚጠራበት የክብር ስም ...... 242

(መ) ፊደል ........................ 243




# መቅድም

ይህንን የመጠሪያና የክርስትና ስም የሚል ጽሑፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ ብዙዎች ወላጆች ለሚወልዱት ልጅ ፅንስ ከተፀነሰ ጀምሮ ስም ለመስየም ሲጨነቁ፤ ስም ፍለጋ ጥያቄ በመጠየቅ እንዲሁም ድኅረ ገጽ (ኢንተርኔት) ውስጥ ገብተው ሲባክኑ በማየቴ ነው።

ለንደን የምትኖረው ወይዘሮ ማርታ ሙሉጌታ ባንድ ወቅት ደብዳቤ በመጻፍ እንዲህ ስትል አሳሰባኝ ነበር።

ለተከበሩ መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት
<u>ለንደን</u>
በቅድሚያ በእግዚአብሔር ስም ሰላምታዬን እያቀረብኩ አንድ ጉዳዬን በተመለከተ ላስቸግሮት።

በአሜሪካ አገር በሜሪላንድ ግዛት የምትኖር እኅቴ በቅርቡ ትወልዳለች። ስለምትወልዳትም ሴት ልጅ የመጠሪያና የክርስትና ስም የሚኾን ፈልጊ ብላ አስጨንቃ ይዛኛለች። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመምረጥ ደጋግሜ ባገላብጥም ላገኝ አልቻልኩኝም። አምላክን የሚያመሰግን ቃል ካለ ብዬም ብፈልግ አልተሳካልኝም፤ አባክዎን የሚያውቁት ለሴት ልጅ የሚኾን ስም ካለ ቢነግሩኝ የተለመዱትና ባኹኑ ጊዜ ብዙዎች እየተጠሩበት ያሉትን አይኾንም ብላለች። እናታችን "ስምን መልአክ ያወጣዋል" የሚባለው በዘልማድ አይደለምና ስም ስታወጡ ጥሩ ሥነምግባር ያለውን ቅዱስ ፈልጋችሁ አውጡ ምክንያቱም የሚወለደው ልጅ ቅዱሱን የመምሰል ልቦና እንዲኖረው ትለን ነበር።

ስለዚህ በግዕዝ ቋንቋ የጸሎቴ ፣ የልመናዬ ምላሽ ወይንም አምላክ ስለቸርነቱ፤ ስለ ሰጦታው፣ ስለ መሐሪነቱ፣ የሚያመሰግን ቃል ለስም የሚኾን ካለ አለዚያ ኢትዮጵያዊትነትን የሚያንጸባርቅ ወይም ሌላ በታሪክ የታወቀች ቅድስት ካለች አባክዎትን ላስቸግርዎ።

የርስዎ አክባሪ ማርታ ሙሉጌታ።

ይህ የወይዘሮ ማርታ ሙሉጌታ ደብዳቤ ለዚህ ጽሑፍ አንዱ መነሻ ኾኖኝ ዐዲስ ለሚወለዱ ሕፃናት ስም ፍለጋ ጀመርኩ ። ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው ምርጥ የኾነ የመጠሪያ ስም ለማውጣት ፤ እንዲሁም ምርጥ የኾነ የክርስትና ስም ለማውጣት እና እንዲወጣላቸው በማሰብ ሲጨነቁ አይቻለሁ፤ ስም ለመምረጥ ደግሞ አንድ ነገርን የሚያንጸባርቅና ምክንያቱንም ፣ ጊዜውንም የሚገልጽ መኾን እንዳለበት የታወቀ ነው።

በዓለም ላይ ያለ ኅብረተሰብ ኹሉ በጎሳው፣ በቋንቋው፣ በባህሉ ስም ይሰይማል ። በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ቋንቋ ብዙ የተለያየ የነገድ ስም አለ ፤ ኹሉም ልጅ ሲወልድ ትርጉም የሚሰጠውንና የሚሰይምበት ለምን እንደኾነ የሚያመለክት ምክንያት አለው ። አንዳንዱ የሚመርጠው ከሙያው፣ ከኑሮው ጋር የተያያዘ ሊኾን ይችላል። የወታደር ልጅ ከጀግንነት ጋር የተያያዘ፤ የገበሬ ልጅ ከግብርና ጋር የተያያዘ፤ የካህን ልጅ ከክህነት ጋር የተያያዘ (ቤተ ክህነት)፤ ከተሜው ከከተሜው ጋር የተያያዘ የመጠሪያ ስም መሰየም የተለመደ ነው ። አንዳንዱ አባትና እናት የልጃቸውን ጠረን ተከትለው ሽታዬ፥ ሽቶ፣ መዐዛዬ ፣ የሚለውንም ምርጫ መርጠው ይሰይማሉ። አንዳንዱም ደግሞ ከፈጣሪ ጋራ ያላቸውን ፍቅር ለመግለጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የቅዱሳን ስሞችና በስመ ክርስትና (ጥምቀት) ስሞች መጥራት ይመርጣሉ።

የኢትዮጵያውያን የመጠሪያ ስሞች ከዕብራይስጥ፤ ከግእዝ፣ ከግሪክ ፣ ከዐማርኛ ፣ ከኦሮምኛ ፣ ከትግሪኛ ፣ ከጉራግኛ ፣ ከዶርዝኛ ፣ ከዐረብኛ… ከሌሎችም ነገዶች የተዋሐደ ፣ የተወራረሰ ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከአባት ጋር ሲገጥሙ ቅኔ ለበስ የሴትና የወንድ ስሞች በምሳሌነት ተጠቅሰው ይገኛሉ ። የኢትዮጵያውያን ስሞች በአብዛኛው በተውላጠ ስም ላይ የተመሠረቱ ናቸው ።

ለምሳሌ፦ <u>ብርሃን</u>፥ <u>አምባ</u> እና <u>ገበያ</u> በሚለው ዘር <u>ተውላጠ ስም</u> ሲተካ ይህንን ይመስላል።

| <u>ተውላጠ ስም</u> | | | |
|---|---|---|---|
| እኔ ፤ | ብርሃኔ | አምባዬ | ገበያዬ |
| እሱ ፤ | ብርሃኑ | አምባው | ገበያው |
| እሷ ፤ | ብርሃኗ | አምባዋ | ገበያዋ |
| አንተ | ብርሃነህ /ብርሃን/ | አምባነህ /አምባ/ | ገበያነህ /ገበያ/ |
| አንቺ | ብርሃነሽ /ብርሃን/ | አምባነሽ /አምባ/ | ገበያነሽ /ገበያ/ |
| እነርሱ፤ | ብርሃናቸው | አምባቸው | ገበያቸው |

ለሴትም ለወንድም የወል መጠሪያ የኾኑ ስሞችም አሉ ።
<u>ለምሳሌ</u>፦ አንተ እና አንቺ በሚለው ተውላጠ ስም ብርሃን፣ አምባ እና ገበያ ለወንድም ለሴትም ጾታ ይኾናል ማለት ነው ። በተጨማሪ መሠረት፣ መዓዛ፣ ቀለመወርቅ፣ ኒቫን፣ ተቋም… ሌላም ብዙ የወል መጠሪያ ስሞች አሉ።



የመጠሪያ ስም የሚኾኑ ስመ ክርስትና፣ ስመ ሀገር፣ ስመ ግብር፣ ስመ ባሕርይ ፣ ስመ ተቀብዖ ፣ ስመ ደብር ፣ ስመ አዕዋፍ ሌሎችም በመጠሪያነት ተለውጠው ሰዎች ይጠሩበታ።

ለምሳሌ አንበሳው፣ አውራሪስ፣ ስመ ባሕርይን ፤ የኃያልነት ባሕርይን ያመለክታል። ሊባኖስ ፣ ደብሬ ፤ ስመ ደብር ሲኾን ታላቅነትን ያመለክታል። ዮርዳኖስ ፣ ዐባይ ስመ አፍላግ ሲኾን ታላቅነትን ኀያልነትን ያመለክታል። እስራኤል ፣ ኢትዮጵያ ስመ ሀገር ፤ አሞራው፣ ርግበ ስመ አዕዋፍ ናቸው ።

ቅጽል ተጨምሮበትም የሚሰየሙ ስሞች አሉ ። ጥሩ-ወርቅ ፣ አምደ ወርቅ ፣ አሰፋ-ወሰን፣ ዓለም-ሰገድ… ሌሎችም ።

ሌላው በኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሥርዐት ጥምቀተ ሲፈጸም ከእግዚአብሔር ልጅነት ማግኘቱን የሚገልጽ መጠሪያ ስም ወይም የክርስትና ስም ይሰጣል። ይህም ስያሜ ጥምቀት ሲጠመቁ በዋለው ቅዱስ ስም ላይ ተጨማሪ ቅጽል በማስገባት ነው (ሉቃ.10፥20፤ ዘፀ. 32፥32)።

ለምሳሌ አበበ በክርስትና ስሙ ኀይለ ሚካኤል ሊባል ይችላል። በምዕራባውያን ዘንድ ግን የክርስትና ስም በቀጥታ የዓለም ስም እና ከቤተሰብ የወረደ የመጠሪያ ስም ይኾናል ፤ ያለ ቅጽል በነጠላው ማይክል (ሚካኤል) ፤ ጆርጅ (ጊዮርጊስ)፣ ጆን (ዮሐንስ) ብሎ መጥራት የተለመደ ባህል ነው።

በርግጥ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አልፎ አልፎ የክርስትና ስም ያለቅጽል የተሰየመም አለ ። በነጠላው ያለ ቅጽል የሚጠሩ ጳጳሳት፣ ማዕርግ ጵጵስና ሲሰጣቸው ብቻ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያሉ የቅዱሳን መጠሪያ ስም፤ የክርስትና መጠሪያ ስም፤ የቤተ ክህነት የመጠሪያ ስም፣ የቤተ መንግሥት የመጠሪያ ስም ፤ የኢትዮጵያውያን የነገድ ስም ተዘጋጅተዋል። ባጠቃላ ለሚወለዱ ሕፃናት ስም ለመሰየም ይረዳል በማለት ፤

- ወላጆች ለልጃቸው ስም ለመሰየም ምርጫ እንዲኖራቸው፤
- በሆስፒታል ለሚወልዱ በቶሎ ስም ለመሰየም ለሚቸገሩ ፤
- ከአገር ወጥተው በውጭ አገር ኑሯቸውን አድርገው ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር ተቀላቅለው ኢትዮጵያዊ ባህል ለተዘነጋቸው ፤
- ለሚወልዱት ልጅ ስም ለማውጣት ለሚቸገሩ፤

እንዲረዳና ጥቅም እንደሚሰጥ በማሰብ ተዘጋጅቷል ። ኾኖም ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልተካተቱ የኢትዮጵያውያን ስሞችን ለኹለተኛው እትም በጥናት እናቀርባለን የሚል ምኞት አለን።

አዘጋጁ

# ምዕራፍ ፩

## የመጠሪያ ስሞች (ስመ ተጸውዖ)

### (ሀ) ወላጆች የሚሰይሙት ስም

የሰው ልጅ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሲፈጥረው የወል ስም ሰጥቶት ነበር። ይህም የወል ስም "ሰው" የሚል ነው። ሌላ ደግሞ በጾታው የወል ስም ወንድ እና ሴት አለ። ከዚያም የፈጠረውን ወንዱን አዳም ብሎ ጠራ። ሴቷን ደግሞ ሔዋን ብሎ እንደጠራ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጿል ። አዳምና ሔዋንም ከነሱ አብራክ የተፈጠሩትን ልጆች ቃየል ፣ አቤል ፣ ከዚያም ሔዋን በአቤል ፈንታ. እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል የአቤልን ተከታይ ሴት በማለት የመ ጠሪያ ስም በመስጠት መሰየም ጀመሩ (ዘፍ. 4፥25)።

ወላጆች ልጃቸውን የሚጠሩበትን ስም መሰየም ከአዳና ከሔዋን ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው።

ማንኛውም ሰው በአገሩ ባህል፣ በቋንቋው ፤ በሃይማኖቱ ረገድ ለልጁ መጠሪያ ስም ይሰይማል። እንዲሁም ደግሞ ኹሉም በሙያው የወታደር ልጅ የጀግንነትን የሚያንጸባርቅ ፤ የካህን ልጅ እምነትን የሚያንጸባርቅ፣ የገበሬ ልጅ ግብርናን የሚያንጸባርቅ ሌሎችም በዚሁ መልክ ለልጆቻቸው ይሰይማሉ።

አንዳንድ ጊዜ ወቅቱን፣ የኑሮውን ገጠመኝ ተከትሎ ወይም የወደፊት የልጁን ዕጣ ፋንታ ነጋሪ ኾኖ የሚሰየም ስም አለ። በረኃብና በጥጋብ ዘመን፤ በመከራና በደስታ ዘመን፤ በጦርነትና በሰላም ዘመን ወላጅ ስም ይሰይማል።

ለምሳሌ አጋረደች ወይም ጋረደው በማለት ወቅቱን አስታኮ ስያሜ ይሰ ጣል፤ ከመከራ ሰወረ(ች) ሊኾን ይችላል ። እናቱን ከሞት ያዳነ ሕጻን ከኾነ ደግሞ አዳነ ፤ ሴት ከኾነች አዳነች በማለት መጥራት የተለመደ ነው ። አንዳ ንዴም የተወለደው ልጅ ታሞ ሊሞት ነው አይተርፍም ከተባለ በኋላ ከሞት ተርፏል ለማለት ተረፈ ይሉታል። ሀብት የትገኘ እንደኾነ፤ ሀብታሙ፣ አዱኛ፣ ንዋይ፤ ክብረት እየተባለ ይጠራል።

የፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ ደራሲ ዐዲስ ዓለማየሁ የመጽሐፉን ከፍተኛውን ገጸ ባሕርይ የሚጫወተውን በዛብህ የተባለውን ሲገልጹ ከተወለደ



ጀምሮ አምስት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ጤና ስላልነበረው ፥ በሽታው ስለ በዛበት ይህ ስም መጠሪያው እንዲኾን የተመረጠለት ነው ይላሉ ።

ጠብ በቤት፣ በዘመድ አዝማድ እና በጎረቤት ገብቶ ሲኖር ልጅ በመወ ለዱ ሰላም ከመጣ ሰላም (ሰላሙ) በማለት ይሰየማል ወይም ደግሞ አማን ብሎ መጥራት የተለመደ ነው ። ይህንም ሲባል ደግሞ ሰላም ተብለው የሚጠሩ ኹሉ ወላጆቻቸው የተጣሉ ነበሩ ተብሎ ትርጓሜ ሰጥቶ እንዲታሰብ ማለት አይ ደለም ።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ከወቅቱ ጋር የሚስማማ ብዙ ስም ተሰይሟል ። ለምሳሌ ሳይታሰብ ጠላት ልጁ ሲወለድ በእኩል የደረሱባቸው ቤተሰቦች ልጃቸውን ዠቅ-አለ ብለው ሰይመውታል። በጦር ሜዳ ውጊያ ጀግናዋ ዐርበኛ ከበደች ስዩም የወለደችውን ልጇን ታሪኩ አበራ ብላዋለች። በጣሊያን ወረራ ዘመን ይሰየሙ የነበሩ ስሞች አዳንዶቹ ከጀግንነት ጋር ፤ ከበቀል ጋር የተያያዙ ነበሩ ። ለምሳሌ ይለይለት ፣ ግፋው ፣ ጠቅጥቃቸው ፣ ታጠቅ ፣ ታፈረ ድንበሩ ፣ ደምሳቸው ፣ ሽጉጤ ... የመሳሰሉ ነበሩ ።

የዐፄ ኀይለ ሥላሴ መንግሥት ተቀይሮ የደርግ መንግሥት ቦታውን በያ ዘበት ዘመን የተወለዱ ልጆች አብዮት ፣ አንድነት ፣ ወዛደር እየተባሉ ተሰይ መዋል። በተቃራኒው ደግሞ አቶ ይንገሡ የተባሉትም የጎጃም ሰው ልጃቸውን አስከጊዜው ብለው ሰይመውታል።

<u>በእስራኤላውያን</u> ዘንድ ስም ሲሰየም ጠባይን፣ ግብርን (ሥራን) ወይም የቤተሰብ ኹኔታን የሚገልጥ ኾኖ ይሰየም ነበር።

ያዕቆብም ሲወለድ ዞሮ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ሲወጣ አዋላጂቷ የቀ ደመውን የያዕቆብ አውራ ጣት አሰረች በዚህ ጊዜ እሰናከይ ተብሎ ተሰየመ። በዚህ አይነት የተሰየሙ ብዙ ስሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። (ዘፍ. 25፥26 ፤ ዘፍ. 38፥27)

በአንድ ቀን ውስጥ የተለወጠው ስም የብንያም ነው ፤ እናቱ ራሔል ምጥ ይዟት በተጨነቀች ጊዜ አዋላጂቱ አትፍሪ ወንድ ልጅ ነው አለቻት ፤ እርሷም ጭንቁ በገዘቶባት ነበርና ቤንኦኒ አለችው። ይህም ማለት የሐዘኔ ወይ የጭንቀቴ ልጅ ማለት ነው። ወዲያው እንደተገላገለች ዐረፈች፤ አባቱ ያዕቆብ ግን ብንያም (ዕብ) አለው። ትርጒሙም የቀኝ እጅ (የማን) ወይም የደቡብ ልጅ ዕድለኛ ማለት ነው (ዘፍ. 35፥18 ፤ 24) ። የያዕቆብና የራሔል ልጅ ታሪክ ደስ የሚያሰኝ እንዲሁም ከቤተሰቡ የመጨረሻ በአባቱና በወንድሞቹ ተወዳጅ ስለ ነበረ ይመስላል ብዙ ኢትዮጵያውያን ብኒያም በማለት ለልጃቸው ስም ይሰይ ማሉ ።

ይሥሐቅ የሚለው ስም ኹኔታዎችን ተከትሎ የተሰየመ ስም ነው ። ይህ ስም የወጣው ሣራ በተገበኘችበት ጊዜ ስለሣቀች ነው ። (ዘፍ.17፥17 ፤ 18፥12 ፤ 21፥3)

ሙሴም የፈርኦን ሴት ልጅ ልዕልቲቷ ከባሕር ስላገኘችው "ከባሕር የተገኘ" ስትል ሙሴ ብላ ሰየመችው (ዘጸ. 2፥10)።

ሳሙኤልም በእናቱ ጸሎትና ስእለት የተወለደ ስለነበር ፤ ጸሎቷ ስለተሰማ "እግዚአብሔር ሰማኝ ስትል" ሳሙኤል አለችው ።(1ኛሳሙ. 1፥20) (በዕብራይስጥ ኤል ማለት እግዚአብሔር ማለት ነው)

ታቦተ ጽዮን በፍልስጥኤማውያን ስትማረክ የእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤል ተገፈፈ ወይም ክብር ራቀ ስትል የፊንሐስ ሚስት የወለደችውን ልጅ ኢካቦድ (ክብር ራቀ) ብላ ሰየመችው (1ኛ ሳሙ. 4፥21)። የያዘው ትርጕም ደስ ስለማያሰኝ በዚህ ስም ሰዎች ሲጠሩበት ተሰምቶ አይታወቅም ።

በቅዱስ መጽሐፍ በበጎነታቸው እና በጥሩ ትርጕም የሚታወቁ ስሞች ተለውጠው ነውርና መጥፎ ምግባራት የነበራቸው ሰዎች ብዙዎች ነበሩ ። በመጥፎ ተግባራት የታወቁት ሰዎች ፤ በአስከፊ ሥራቸው የተነሣ ትውልድም ሳይጠራባቸው ይኖራል።

ለምሳሌ፦ ቃየል መሥዋዕቱን በንጽሕና ስላላቀረበ በእግዚአብሔር ዘንድ አልተወደደም፤ ይህም አልበቃ ብሎት ወንድሙን አቤልን ስለገደለ የተረገመ ኾነ። ስለዚህ ቃየል ብሎ የሚሰይምና የሚጠራ የለም ። እንዲሁም ሒትለር ብሎ የሚሰይም የለም። ከሴቶችም ሚልኮል ፣ ደሊላ ብሎ የሚጠራ የለም (ዘፍ. 4፥8 ፤ 2ኛ ሳሙ.6፥16-23 ፤ መሳ. 16፥4–22)።

ከዳዊት ልጆች በኵር የኾነው አምኖን እኅቱ ትዕማርን አስገድዶ ስላስነወራት የናት ልጅ ወንድሟ አቤሰሎም በዚህ አሳፋሪ ድርጊቱ በንዴትና በበቀል አስገድሎት ሸሸ። ይህም ቤተሰቡን አበጣበጠ። በዚህ ክፉ ሥራው የተነሳ በአምኖን ስም አምኖን ብሎ የሚሰይም የለም (2ኛሳሙ. 13፥1 ፤ 3፥2–5)።

እዚህ ላይ ሊታሰብበት የሚገባ ልጆች መጥፎ ምግባር ይዘው እንዳያድጉ ወላጆች ኀላፊነት አለባቸው ። በተለይም እናት ልጇን ለማስተማር የቅርብ ሰው ነች። ይህም ጢሞቴዎስ በናቱ በኤውንቄ በአያቱ በሎይድ የተሰጠው ትምህርት፤ የወረሰው መልካም ሥነ-ምግባር ለኋላ ጊዜ ለኑሮውና ለመንፈሳዊ ሥራው ጠቅሞታል፤ ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ መስክሮለታል ። ለልጆች ጥሩ ስም ብቻ ለመሰየም መፈለግ ሳይኾን አስተዳደጋቸውንም መከታተልና መንከባከብ ያስፈልጋል (2ኛ ጢሞ 1፥5፤ የሐ. ሥራ 16፥1)።



በሕይወት አጋጣሚ የደረሰውን፤ ጠባይን ወይም ድርጊትን፣ ማኅበራዊ ኑሮን፣ ቦታን የሚያንጸባርቁ ስሞች ይሰየማሉ ። ኹሉም ደስ የሚለውንና ትርጕም የሚሰጠውን ስም ይሰይማል። ሌሎችም ሃይማኖቶች ለነሱ እንደሚስማማቸው በራሳቸው መንገድ ይሰይማሉ።

## (ለ) "ስምን መልአክ ያወጣዋል"

ስምን መልአክ የሚያወጣው መኾኑን እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቀው ለሰው ልጆች የተሰጠ ፍጹም ምስጢር ነው። ወንድ ወንድ ኾኖ እንዲፈጠር ፤ ሴት ሴት ልጅ ኾና እንድትፈጠር የኾነበት ምስጢር የእግዚአብሔር ምስጢር ነው። እንዲሁም ስም የመለኮታዊ ባሕርይ ምስጢር ነው።

ለመውለድም ኾነ ለመወለድ ምስጢር እንደኾነ ኹሉ ፤ ከአባት አብራክ ከእናት ማሕፀን ሳይደርስ ስለግብሩ ትንቢት መናገር መለኮታዊ የኾነ ከሰው ኀሊና በላይ ነው ። ይህ ስጦታ ግን የእግዚአብሔር እንደራሴዎች ለኾኑት ቅዱሳን መላእክት ይቻላቸዋል ። ይኽን ምስጢር ማንም በምርምር ሊረዳው የማይቻል ነው ። ኾኖም ግን ቅዱሳት መጽሐፍት በሚያስረዱን መንገድ ስምን መልአክ እንዲሚያወጣው እናያለን (ሉቃ. 1፥11 ፤ ማቴ. 1፥21)።

## (፩) ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ መለኮት

በቅዱስ ወንጌል ካህኑ ዘካርያስ በሰሞን ተራው በቤተ መቅደስ ኾኖ ዕጣን ሲያጥን ሕዝቡም ሲጸልዩ የጌታ መልአክ ተገለጸለት ።

መልአኩም ጸሎትህ ተሰምቷልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላ ይኾንልሃል ። በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል። በጌታ ፊት ታላቅ ይኾናል ፤ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ፤ ገና በናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል አለው።... (ሉቃ. 1፥11) ዘካርያስም ለመልአኩ የሰጠው መልስ – እኔ ሽማግሌ ነኝ ምስቴም በዕድሜዋ አርጅታለች ይህን በምን ዐውቃለሁ ? መልአኩም መልሶ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ እንድናገርህም ይህችን የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንክ ይህ ነገር እስከሚኾን ድረስ ድዳ ትኾናለህ መናገር አትችልም አለው።

የኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ ወንድ ልጅም ወለደች ጎረቤቶቿም ዘመዶቿም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከርሷ ጋር ደስ አላቸው ። በስምንተኛው ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት

ወደዱ፤ እናቱ ግን መልሳ አይኾንም ዮሐንስ ይባል አለች። እነሱም ከወገንሽ
ማንም በዚህ ስም የተጠራ የለም አሏት ፤ አባቱንም ማን ሊባል እንደሚወድ
ጠቀሱት፤ ብራናም ለምኖ ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ ። ኹሉም አደነቁ።
(ሉቃ.1፥57 - 64)።

### (፪) አፄ መሶበወርቅ

**ዐፄ ድልነአድ** (902 -913 ዓ. ም.) በቤተመንግሥታቸው መራ ተክለሃይ
ማኖት የሚባል የላስታ እና የአገው ሰው አጋፋሪ ነበራቸው ። **ዐፄ ድልነአድ**
ሴት ልጅ ከወለዱ ለመንግሥታቸው መጥፋት ምክንያት እንደምትኾን ትንቢት
ይነገር ስለነበር ሴት ልጅ በመውለዳቸው በመንግሥታቸው ሥጋት አደረባቸው።
ትንቢቱ እንዳይፈጸምባቸው ለሌሩ ሳትታወቅ ቶሎ ሊያጠፏት አሰቡ። ለዚህም
ሰው እንዳይሰማባቸው ሕፃኗን በመሶበወርቅ አድርገው ለታማኙ አጋፋሪያቸው
መራ ተክለሃይማኖት መሶበወርቁን ሳይከፍት ወደ ወንዝ እንዲጥል ሰጡት

መራ ተክለሃይማኖት ወንዝ ሳይደርስ ድምፅ ስለሰማ መሶቡን ከፍቶ
ቢያይ ሕፃን ልጅ አገኘ ። መሶቡን ብቻ ወደ ወንዝ ጥሎ ሕፃኗን በድብቅ እን
ዲያሳድጉለት ራቅ ወዳሉት ዘመዶቹ በአደራነት አስቀመጣት። ከብዙ ዓመታት
በኋላ ላቅመ ሔዋን በደረሰች ጊዜ የቅርብ ወዳጅ ታማኝ በመኾኑ ልጃቸውን
ይድሩለት ዘንድ ንጉሡን ዐፄ ድልነአድን ለመነ ። ንጉሡም ከዘመን ብዛት የተ
ነሳ ሴት ልጅ መውለዳቸውን ረስተውት ነበር። ወደ ወንዝ እንዲጥል ከታዘዘው
መሶብ ውስጥ ልጅቱን እንዳገኘና እንዳሳደጋት ነገራቸው። ንጉሡም ብዙ ሰዓት
ከሰቡ በኋላ ከጃቸው እንዳልወጣች ስላወቁ መልካም ነው ፈቅጃለሁ ሰርጓን
ደግሰን ስለምንድራት አምጣልን አሉት፤ እሱም ለማምጣት ተሰናብቶ ወደዘመ
ዶቹ ኼደ። ለዘመዶቹም ታሪኩን ነገራቸው ። ዘመዶቹም በዚህች ሕፃን የዚህ
ዓይነት ጭካኔ ቀደም ብለው የፈጸሙባት ያለ ምክንያት አይደለም፤ አንተም
ታማኝነትኽን ስላፈረስክ ቅጣት ያገኝሃል ፤ ልጅቱንም አንተንም ያጠፏችኋል
አሉት።

መራ ተክለሃይማኖት የዘመዶቹን ምክር ከሰማ በኋላ ወደንጉሡ ቤት
መመለስ ፈራ ። ንጉሡም ኼዶ በመቅረቱ በመልቀቃቸው ተጸጸቱ ። ወታደሮቻ
ቸውን ፈልገው ይዘው እንዲያቀርቡት ላኩ ። ወታደሮቻቸው ከመራ ተክለሃይ
ማኖት ወገኖች ጋር ታላቅ ጦርነት አደረጉ ። የንጉሥ ወታደሮች በሽንፈት ሸሽ
ተው ወደ ንጉሡ ኼዱ ። ራሳቸው ንጉሡ ወደ ጦርነቱ ገቡበት ጥቂት እንደተ
ዋጉ ወታደሮቻቸው ስለደከሙባቸው ወደ አንድ ተራራ አመሩ ። መራ ተክለሃ
ይማኖት ሕዝቡን አረጋጋ። ንጉሡም ረዳት ስላላገኙ ወደ ሸዋ ሸሹ ። መራ ተክ



ለሃይማኖት የንጉሡን ርቆ መኼድ ባወቀ ጊዜ ልጅቱን አስመጥቶ ታላቅ ሰርግ
አድርጎ አገባት። በኋላ ሥልጣን መንግሥቱን ይዞ ተቀመጠ ።

ወደወንዝ ልትጣል በመሶበወርቅ የተወሰደችው **ልዕልት መሶበወርቅ**
ተብላ መጠራት ጀመረች። ንጉሡ ሸሽተው ስለኼዱ መራ ተክለሃይማኖት ድልን
ስለተቀዳጀ በግእዝ "ዘአጉየየ መራ ለድልነአድ" ተባለ ። ትርጕሙም መራ ድ
ልነአድን አሸሸው ማለት ነው። ዘአጉየየ የሚለው ስያሜ ስመ መንግሥቱ አደ
ረገው። ዛጉዬ የሚለው ዘአጉየየ ከሚለው የመጣ እንደ ኾነ ይነገራል ። መራ
ተክለሃይማኖት እና ንጉሡ ድልነአድ የተዋጉበት ቦታ እስከዛሬ መራ በመባል
ይታወቃል ። ይህ ከኾነ ንግሥና ከቀዳማዊ ምኒልክ ከሰሎሞናዊ ዘር በቴጌ መሶ
በወርቅ አማካኝነት ተላልፏል ማለት ነው።

### (፫) ቅዱስ ላሊበላ

መራ ተክለሃይማኖትና **ልዕልት መሶበወርቅ** ከወለዷቸው ልጆች አንዱ
ዣንሥዩም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኾነ ።

**ቅዱስ ላሊበላ** ከንጉሠ ነገሥቱ ከዣንሥዩምና ከእናቱ **ኬረዎርና** ከተባ
ለችው ከአገው ሴት ታኅሣሥ 29 ቀን 1120 ዓ. ም. ተወለደ ።

**ኬረዎርና** ከላስታ አገው መጥታ በንጉሡ ቤት በአገልጋይነት የተቀመ
ጠች ነበረች። **ኬረዎርና** ማለት ቤተክርስቲያን ማለት ነው። ንጉሡ ዣንሥዩም
ውበቷ ስለማረከው ደረሰባት ልጅም ፀነሰች። በሌሊት በራእይ በዚህች ሌሊት
በማሕፀንሽ የተቀረጸው ሕፃን ፈጣሪውን ለማገልገል የተመረጠ ነው የሚል
ድምፅ **ቅዱስ ሚካኤል** አበሠራት። ጥቂት ቀኖችም እንዳለፉ ፅንሱ እየገፋ
ኼደ። እቴጌ ዕፅፍት የተባለችው የንጉሡ የሕግ ባለቤት መኾን ስለነበረች አል
ወደደችትም ፤ **ኬረዎርናን** ከባድ ሥራ ታሠራት ጀመር። የመውለጃዋ ጊዜ ሲደ
ርስ እንጨት ለመልቀም እኼደችበት ጫካ ውስጥ ወለደችው። **ኬረዎርና** እቴጌ
ዑፅፍት በተንኰል እንደተነሣችባት ስለምታውቅ ሕፃኑን ይዛ ወደ ቤተ መንግ
ሥት ለመመለስ የሚያሠጋ እንደኾነ አሰበች። **ሮሃ** ከተባለው ቦታ ላይ በአንድ
ዋሻ ውስጥ አስተኛችው። እንድትወለድ የፈቀደ ፈጣሪህ ነው፤ ወደ ቤት ወስጄ
ዐይኔ እያየ ከማስገድልህ ሳላይህ ከዚህ ብትሞት ይሻላል ብላ ከዋሻው ውስጥ
ትታው ኼደች ።

ወደ ቤተ መንግሥቱም በደረሰች ጊዜ **ኬረዎርና** ተዳክማ ስለነበር ወደ
ቀች። ይኽንን የሰማ የንጉሥ አገልጋይ እየሮጠ ኼዶ የኾነውን ኹሉ ለንጉሡ
ነገረው። ንጉሡ ወዲያው ለድካሟ ማስታገሻ የሚረዳትን ነገር እንዲያደርጉላት
አዘዘና ስለልጁ ኹኔታ ጠየቃት ። እርሷም የተፈጸመውን ኹሉ ገለጸችለት።
ንጉሡም አዛዡንና አገልጋዮቹን ጠርቶ ትታው ወደመጣችበት በቶሎ ይዘዋት

| | |
|---|---|
| ■ ዋጋዬ እንተነህ ፤ | ዋጋዬ |
| ■ የሠራህ ግሩም ፤ | የሠራሽ |
| ■ ይኹን በፍቃዱ ፤ | ትኹን |
| ■ ግሩም ተሠራ ፤ | ግሩምነሽ |

የሚሉ ስሞች በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ ውስጥ ይገኛሉ ።

ሰዎች እየተጠሩበት ከአባት ጋር ገጥመው የሚሰሙ ስሞች አሉ።
<u>ለምሳሌ</u>፦

| | |
|---|---|
| ■ ሰማኸኝ በለው | ሰማችኝ |
| ■ ሹመት ሲሻኝ | ሹመቴ |
| ■ አድጎ አይቼው | አድጋልኝ |
| ■ አገሬ ይልማ | አገሬ |
| ■ እውነቱ ገነነ | እውነት |
| ■ ዘላለም እንየው | ዘላለም |
| ■ ይገደብ ዓባይ | ትገደብ |
| ■ ግርማቸው አማረ | ግርማዊ |
| ■ ጸጋ ቸኮለ | ጸጋ |
| ■ በጸጋ አንዳርጋቸው | በጸጋሽ |
| ■ ፍቅር ዐዲስ | ፍቅር |
| ■ ፍቅር አሸናፊ | ፍቅሬ |

ሌሎችም ከባት አልፈው አያት ተቀናጅተው ቅኔያዊ ምስጢር ፤ ዐረፍተ ነገር የሚሠሩ ስሞች አሉ።

<u>ለምሳሌ</u>፦ ቢወጣ እያለቅበት ብሩ።
ተመስገን ዘላለም ደሳለኝ።
ቃል-ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት።

ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር ካሉት ስሞች የተገናኙ እንደዚሁ የተሰየሙ ስሞች አሉ። <u>ለምሳሌ</u>፦ የሥላሴ ዕለት የተጋቡ ባልና ሚስቶች ባማርኛ የምርምር ቅኔ ሲቀኙ ላቸው ።

ሥላሴ በቤትሽ ገብተው ሲባርኩሽ
ለይኩን ብርሃን የሚባል ልጅ ይሰጥሽ ።

በትንቢቱ መሠረት ልጁ ባመቱ ሲወለድ የተነገረው ተፈጽሟልና ለይኩን ተባለ ማለት ነው። ትርጉሙም እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ሲያበቃ ብርሃን ይኹን አለ ማለት ነው። በዚህ አይነት የሚሰየሙ ስሞች ብዙ ናቸው (ዘፍ. 1፥16)።

- ■ ታመነ አብርሃም (ዘፍ. 18፥)
- ■ ኅይመተ አብርሃም ፤ (ለሴትም ይኾናል)



- ■ ነቢዩ ኤርምያስ ፤ ነቢዩ ዳንኤል ፤ ነቢዩ ኢዩኤል .......
- ■ መጽሐፈ ሲራክ ፤ (ለሴትም ይኾናል)
- ■ ግርማ ሞገስ ፤
- ■ በእምነት ደረጀ (ለሴትም ይኾናል)
- ■ ለባሲተ ሞገስ (ለሴት)

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አምላክን ስለችሮታው በማድነቅ ፤ በማፍቀር የሚሰየም ስም አለ <u>ለምሳሌ</u>፦

| | |
|---|---|
| ■ ላመስግነው | ላመስግን |
| ■ አላምረው | አላምር |
| ■ ሰማ-እግዜር | ሰማኝ-እግዜር |
| ■ ሲምር-ጌታ | ሲምርሽ-ጌታ |
| ■ ሰጠኝ-ጌታ (ጌታ-ሰጠኝ) | ሰጠኝ-ጌታ |
| ■ ባንተ-አምላክ | ባንቺ-አምላክ |
| ■ ባሳዝነው | ባሳዝን |

አንዳንድ ጊዜ ከዘመድ ወይም ከጐረቤት ጋር በሚደረገው አለመግባባት፤ የደረሰባቸውን በደል፣ ሐዘንና ጥቃትን ለመግለጽ መልእክቱን በሚወለደው ልጅ አማካኝነት እንዲተላለፍ ይደረጋል ።

| | |
|---|---|
| ■ አስመላሽ | አስመልሺው |
| ■ እንዳርጋቸው | እንድአርጊያቸው |
| ■ እንዳልካቸው | እንዳልሻቸው |
| ■ ዝምበላቸው | ዝምበያቸው |
| ■ ይግረማቸው | ትግረማቸው |
| ■ ደምመላሽ | ደመልሺ |
| ■ ድፋባቸው | ድፊባቸው |
| ■ ጸጥአርጋቸው | ጸጥአርጊያቸው |

- ■ ሽጉጤ መሣሪያን ያመለክታል:: ወደብብቱ ሽጉጥ ያለ ማለት ነው::
- ■ ሽንቁጥ ግረፍ: ጥበስ ማለት ነው (ሽንቁጤ)

ይህን የመሳሰሉ አሉ ፤ ነበሩ።
አንዳንድ ጊዜ ስም ባሕርይን ፣ ግብርን እና ጠባይን ይዞ ሲኼድ ይታያል። "ስም ይመርሖ ኀበ ግብሩ" ስላም ተብላ የምትጠራ ልጅ ሰላማዊ የኾነ ባሕርይ ይታይባታል ማለት ነው ። በርግጥ ይህንን የመሰለው ስም ድምፅን ጎላ አድርገው ቢጣሩት ለሰው ልጆች ደስታን የሚሰጥ መልእክት አለው ። በሕርዩ ሸጋ ነው ሲሉ እንግዳወርቅ ይሉታል።

## (ሠ) የፍቅር እና የቍልምጫ ስሞች

ቍልምጫ ፍቅርን ፣ ማሞገስን ወይም ወዳጅነትን ፣ የሚገልጽ ነው ።
 የይሥሐቅና የርብቃ ልጅ ስሙ ያዕቆብ ነበር። እግዚአብሔር ግን እስራኤል ብሎ በቍልምጫ ስም እንደጠራው በትንቢተ ኢሳይያስ ተገልጿል። እስራኤል ማለት ትርጓሜው "ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ያሸንፋል" ማለት ነው። (ኢሳ. 45፥4 ፤ ዘፍ. 32፡22–32)።

ፍቅርን ወይም ወዳጅነትን ለመግለጽ አንዳንዴ ታላቅ ወንድም ታናሽ እኅቱን በቁልምጫ መጥራቱ የተለመደ ነው። በተለይም ሕፃናትን በቍልምጫ መጥራት የተለመደ ነው። እንዲሁም አንድ ሰው ወዳጁን ሌሎች በማይጠሩት ስም ከፍቅሩ የተነሣ ቢጠራ ያ ስም የቍልምጫ ስም ነው ለማለት ይቻላል።

አብዛኛውን ጊዜ የቍልምጫ ስም የመጨረሻው ፊደል ዬ የሚለውን ያስከትላል ። ብርሃንዬ፣ ማኅሌትዬ… ወይም ደግሞ በኹለት ፊደል የሚጠቀለል ቁልምጫ ለምሳሌ መኰንን የሚለውን መጠሪያ መኩዬ፤ ጌታቸው የሚለውን ጌትዬ (ጌትሽ) ይባላል። አንዳንድ በኹለት ፊደል ሲጠቀለል ለቍልምጫ የማይመችም ስም ደግሞ አለ። <u>ለምሳሌ</u> ፦ አረጋ፣ አረጋይ፣ አርአያ፣ አሮን የሚለውን በኹለት ፊደል ዬ ተጨምሮበት ለማቆላምጥ ቢሉት አይመችም ። ረ ፊደል ባለጌነች ይባላል (ሩ ፣ ሪ ፣ ራ)።

በፍቅር የተነሣ ፍቅረኛሞች ፤ ባልና ሚስት እንዲሁም የሚቀራረቡ ቤተሰቦችና ወዳጆች በዚህ መልኩ እየተቈለማመጡ ፣ ቢሞጋገሱ ፍቅርን ፤ የማኅበራዊ ኑሮን፤ መቀራረብን ይፈጥራልና የሚደገፍ ነው።

አንዳንድ ሰዎች በውጭ አገርም ኾነ በአገር ውስጥ የራስ ባህል ያልኾነውን ስማቸውን ወደ ፈረንጅ ስሞች ቀይረው የሚቆለማመጡ አሉ፤ ጄሪ (ኢየሩሳሌም) ቲጂ (ትዕግሥት) ጆኒ (ዮሐንስን)፤ ጆርጅ (ገብረ ጊዮርጊስን) ፤ ማርዮ (ኀይለ ማርያም) ፤ ማይክ (ኀይለ ሚካኤል) ፤ በማለት በዚህ አይነቱ አጠራር ሲጠራሩ ይሰማል። አውሮፓ ቀመስ በመኾኑ «የሰው ወርቅ አያደምቅ» ያሰኛል

የራሳችን አለን፦ ኢየሩስ (ኢየሩሳሌም)፤ ኤልሲ (ኤልሳቤጥ) ቤቲ (ቤተልሔም) ጂጂ (እጅጋየሁ) ፤ ሩፊ (ወልደ ሩፋኤል) ጉሌ (ጉልላቴ) ማዱ (ማኅደረ) ሌላም ማለት የተለመደ ነው ። ይህ ኹሉ ከፍቅር የመጣ ስለሚመስል ተቃውሞ የለበትም።

ድንገት የሚከሠት ሕፃን ከተወለደ በኋላ እስከሚሰየም ስም ሲፈልጉ ጊዜ በመወሰዱ ሳይታሰብ እንደቀልድ የሚሰየሙ የቍልምጫ ስሞች አሉ።



<u>ለምሳሌ፦</u> በቤተሰብ በመጥራት ተለምዶ ማሙዬ፣ ማሙሸዬ (ማሙሸት) ማሚቱዬ (ማሚቱ)፣ ሚሚ፣ ይባላል። አብዛኛው በኋላ ዕድሜ ላይ ይቀይሩታል

ሮዚና፣ ቤቢ ፣ ቢሲ ፣ ቢጢ፣ ቢግ፣ ቡጫ፣ ሲዲ፣ ቦቢሻ፣ ሙኒሻ፣ ኢሚ ፤ እንዲህ አይነቱ የቍልምጫ ስም አንዳንዴ በዕድሜ ሲጐለምሱ ይቀራል። አንዳንዶችም መልካምነቱን ተቀብለው በዚያው እየተጠሩበት ይቀጥላሉ። ላንዳንዶችም ተጨማሪ የቤት ስም ይኾናል ፤ ባለቤቱ ከወደደው ጉዳት የለውም ። ዋናው ነገር ግን ግራ ከሚያጋባ ስም ጥሪ ወስጥ ከመግባት መጠንቀቅ ይገባል ለማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜም የቤት እንስሳትን ስም ይዞ የሚጠሩበት የቍልምጫ ስሞች አሉ። ለምሳሌ፦ ዉሮ፣ ዉሪ፣ ውርዬ ፤ ቲቲ. ቲቲዬ፣ ቡፒ፣ ኩኩ (ኩኩ መለኮቴ) ። አንዳንድ ጊዜ መጠሪያ ስም ኾኖ የሚቀር አለ። ለምሳሌ፦ ኑኑ - ኑኑሻ ፤ ፋፋ - ፋፋሻ ፤ ቡጡ - ቡጦሻ ፤ ደቦጭ ፣ ቻቻ ፣ ኮኪ ሌሎችም ስሞች አሉ።

አኹንም፤ ያለውን እውነት ለመግለጽ ነው እንጂ ባለቤቱ ከተስማማ፥ ኅብረተሰቡም ከለመደው ለመጠራት ኾነ ላለመጥራት የሚከለክል ምንም ነገር የለም። መጠራት ወይም አለመጠራት የራስ ምርጫ ነው ። ነገር ግን እነዚህ የቍልምጫ ስሞች ለምሳሌነት ያኽል የተጠቀሱት ወላጆች ስምን ለልጆቻቸው ሲያወጡ ከመጀመሪያው መንፈሳቸውን ደስ የሚያሰኝበትን መሰየም እንዲችሉ ነው ። ልጆች ግን ለሚሰየምላቸው ስም ለወላጆች ሽልማት ወይም ምስጋና ሲሰጡ ታይቶ አይታወቅም ፤ ከልተደሰቱበት ግን ራሳቸውን እሳምነው እስከሚለውጡ ድረስ ጊዜ ይወስድባቸዋል ።

ልጅ ከተወለደ በኋላ በስም ስያሜ ብዙ ጊዜ አለመስማማትና ይኹን አይኹን የሚል ወላጆችም (ባልና ሚስት) የየራሳቸው ስም ማውጣት የተለመደ ነው ። አንዳንዴም እቤተሰብ ውስጥ የቅርታ ስሜት መኖሩና እንግዳ የኾነ ስም ቶሎ አለመለመዱ እና ተቀባይነት አለማግኘቱ የተለመደ ነው ። ወላጆች ግን የሌሎችን ትችት ሳይፈሩ ለነሱ መንፈስ ደስ ያላቸውን ቢያወጡ ቀስ እያለ ይለመዳል፥ ተቀባይነትም እያገኘ ይኼዳል ማለት ነው።

| | |
|---|---|
| ■ ዲበ-ኩሉ | ከኹሉ ላይ (መዝ. 96(97)፥9) |
| ■ ኀሑ-ጽባሕ | የማለዳ ኀሕ (ቅዳ. ማር) |
| ■ ጥቀ-ኄር | ቸርነትህ እጅግ በዛ (መዝ.72፥1) |
| ■ ጥዑመ-ልሳን | አንደበቱ የሚጥም (ያሬድ) |
| ■ ፈለገ-ሕይወት | የውሃ ምንጭ |
| ■ ፈለገ-ሰላም | የሰላም ምንጭ |
| ■ ፍሬ-ሠናይ | ጥሩ ፍሬ |

<u>የቤት ጸታ</u>

| | |
|---|---|
| ■ ለኪ ይደሉ | ላንቺ ይገባል (አንቀጸ ብርሃን) |

በጣሊያን ወረራ ጊዜ የቅኔ ትምህርት አስተማሪ የነበሩ አንዲት ምሁር ሴት ይጠሩበት ነበር።

| | |
|---|---|
| ■ ሐረገ-ወይን | የወይን ሐረግ (መሐ. 1፥6) |
| ■ ሥነ-ሕይወት | የሕይወት ውበት |
| ■ ሰብለ-ወንጌል | የወንጌል አሸት |
| ■ ነገደ-እስራኤል | የእስራኤል ነገድ (ዘፍ. 49፥7) |
| ■ አስካለ-ወይን | የወይን ዘለላ (መሐ. 4፥29) |
| ■ አንቀጸ-ብርሃን | የብርሃን መውጫ (ወዳ. ማ) |
| ■ አፀደ-ወይን | የወይን ተክል (መሐ. 1፥6) |
| ■ ዕንቁ-ብርሃን | የሚያበራ ዕንቊ (ዘጸ. 28፥18) |
| ■ ኩብኩብ | ሠርግ (ዮሐ. 2፥1) |

## (ሸ) የተዋሐዱ የመጠሪያ ስሞች

ኢትዮጵያውያን በባህልም ፣ በዘርም በመዋሐድ ፣ በመጎራበትም ፣ ተደባልቀው አምቻና ጋብቻ ኾነው ከጥንት ጀምሮ እስከ ቤተመንግሥት ድረስ ተሳስረው ኖረዋል። በየዘመኑ የተነሡትም ነገሥታት ከኹሉም ዘር በመደባለቅ ተዋልደዋል፣ ወልደዋል፣ ተዋርሰዋል ፤ በዚህም የተነሣ የመጠሪያ ስሙም አብ ዛኛው የጋራ ስሞች ኾነዋል። ለምሳሌ እኹሉም ዘንድ ከሚታወቁት ሀገራውያን ስሞች፤ ከበደ (ከበደች)፣ በቀለ (በቀለች) ጉግሳ፣ ጌታቸው፣ ተሰፋዬ፣ ሸዋዬ... ሌሎችም የሚጠሩባቸው የተዋረሱ አሉ።

የወንዶች እና የሴቶችን ስሞች ግእዝ (ግእ)፣ ዐማርኛ (ዐማ)፣ ኦሮምኛ (ኦሮ)፣ ትግርኛ (ትግ)፣ ጉራጌኛ (ጉራ)፣ ዶርዜኛ (ዶር)፣ ዕብራይስጥ (ዕብ) ፣ ግሪክ (ግሪ) ፣ ዐረብ (ዐብ)... ከየትኛው ክፍል ተሰባሰበው በተቀራራቢ ትርጉም ቀርበዋል።



በዚህ ዝግጅት ኹሉንም የኢትዮጵያውያንን የመጠሪያ ስሞች በማሟላት ያካትታል ማለት አይቻልም ፤ ነገር ግን ለማስታወሻነት ጠቃሚነት ይኖረዋል በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን በመጨመር፤ በዘመነ ነገሥታት፣ በዘመነ መሳፍንት ፣ በዘመነ አንድነት እና በዘመነ ኮሚኒስት በነበሩት የታሪክ ጊዜያት የተሰየሙትን እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ፣ የታሪክ ሰዎች ፣ ለዘመናት ሲጠሩባቸው የኖሩትና አኹንም ብዙዎች እየተጠሩበት ያለውን ሲጠሩበት የተሰማውን በዋቢነት በመጥቀስ ማብራሪያ ጭምር በመስጠት በማሰባሰብ በዚህ ጽሑፍ ሰፍረዋል።

ብዙዎቹ የታሪክ ሰዎች ሞክሸ ስሞች ስላላቸው የአንዱን በቻ በመውሰድ ተጽፈዋል።

መጠሪያ ስሞች ከአባት ስም ጋር ሲገጥሙ በምስጢር መንታ ትርጉም ወይም የምርምር ቅኔ እንዲሰጥ በማድረግ ቀርቧል። ይህንም ደራሲው አንባቢ ሳይሰለች እንዲመራመርበት ለማድረግ ከመኾኑ በስተቀር ማንንም የግለሰብ ስም አይወክልም። የሚወክለው የኢትዮጵያውያንን ስም ነው። ትርጉምና ትንታኔው ለመንደርደሪያ ያህል ቢጠቀስም ፤ የትርጉም አሰጣጥ እንዲሁም ምርጫ ግን የባለቤቱ ወይም የወላጅ ነው ።

የስም አወጣጥ እና አተረጓጐም እንደ ጊዜ ፣ እንደ ሰው ኹሉ የተለያየ አመለካከት ሊሰጠው ይችላል። ስለዚህ ፤ ደራሲው በመሰለው መንገድ ትርጉም ያላለቀ ቀጣይ መኾኑን የሚያመለክት <u>ነጠላ ጥቅስ</u> (...።) አድርጓል።

237.**ሰብለ** (ግእ)
አሸት ዘረዘረ ደረሰ ጨረሰ ማለት ነው።
ያባት ስም እሸቱ ቢል ይገጥማል።
**ሰብለገነት - ሰብሉ - ሰብለ-ማርያም**

238.**ሰንበት (ሰንበተ)** (ዕብ)
ማረፍ፣ ማቆም ማለት ነው (ዘጸ. 20፥8)።
**ሰንበቱ - ሰንበታ - ሰንበቶ** (ኦሮ)

239.**ሰንደቅ** (ግእ)
ክብር ያለው ዓላማ የባንዲራ መስቀያው።
**ሰንደቁ - ሰንደቄ**

240.**ሰከወርቅ**
ወርቅ አጠለቀ ...።
ያባት ስም ማዕርጉ ቢል ይገጥማል።

241.**ሰወሃሪ** (ጉራ)
በክፉ ቀን ውለታ አድራጊ ማለት ነው።

242.**ሰውነት**
ሥጋና ነፍስ መኾን (ማቴ. 5፥29)።
ያባት ስም ሙኩሪያ ቢል ይገጥማል።
**ሰውዓለም - ሰውአገኝ - ሰዋገኘሁ**
**ሰውሐረግ - ሰውመኾን - ሰውበሰው**
**ሰውአለ - ሰውአለኝ**

243.**ሰይፉ**
በልማድ ሴፉ ይባላል።
በኹለት ወገን ስለት ያለው። የእግዚአብ
ሔርም ቃል ምሳሌ ነው (መዝ. 149፥6 ፤
ኤፌ. 6፥17 ፤ ዕብ. 4፥12)።
በዚህ ስም የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን
አንዱ ። የንጉሥ ኀይለ መለኮት ታናሽ
ወንድም የዐፄ ምኒልክ አጎት ፤ አቤቶ
ሰይፉ ሣህለ ሥላሴ ተጠርተውበታል።
**ሰይፍ - ሰይፌ - ሰይፌ ሥላሴ** (ክር)

244.**ሰገነት**
በቤት ጣራ ላይ የሚሠራ መናፈሻ ቦታ
ወይም ማደሪያ ክፍል (2ኛ.ሳሙ. 11፥2 ፤
ዳን. 4፥29 ፤ 1ኛ ነሥ. 17፥19)።

245.**ሰገደ**
በአክብሮት ማጐንበስ ማለት ነው።
(ኢሳ. 46፥2) **ሰገዱ - ሰገዴ - ሰጊድ**

246.**ሰጠኝ**
አበረከተልኝ ፣ በጄ አደረገልኝ ...።
ገንዘብ፣ የልፋት ዋጋ፣ ሀብት ...።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።
**ሰጠ - ሰጠነው - ሰጠኸኝ - ሰጡ**

247.**ሰጥአርገው** (ሰጣርጋቸው)
ዝም አሰኛቸው ፣ አረጋጋቸው ።
ያባት ስም ግርማኹን ቢል ይገጥማል።
**ሰጥአለ - ሰጥአርጌ - ሰጥአርጋቸው**

248.**ሰፈረወርቅ - ሰፈረ**
በሚዛን ፣ በእንቅብ ፣ በቁና ሞላ።
ያባት ስም ምንዳዬ ቢል ይገጥማል።

249.**ሱራፌል** (ዕብ.)
ስመ ነገድ ፤ በራእይ ለኢሳይያስ የታዩ
በእግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ የሚያገለ
ግሉ ስማያውያን ልዑላን ሊቃነ መላእ
ክት (ኢሳ. 6፥1–7)።

250.**ሲራክ** (ዕብ.)
ጸሐፊ (መስመር) ማለት ነው ።
የምክር ቃል የያዘ መጽሐፍ በኢያሱ
ሲራክ በራሱ እንደተጻፈ ገልጧል።
የጥበብ ኹሉ መገኛው ከእግዚአብሔር
ዘንድ ነው ይላል (መጽ. ሲራ.1)።



251.**ሲሳይ** (ግእ)
ምግብ፣ ማንኛውንም በረከት ያመለክታል
ሲሳይ ከርሻና ከእንስሳ ይገኛል ።
ዘይውህብ ሲሳየ ለኵሉ ዘሥጋ። ትርጉም፤
ለሥጋ ኹሉ ምግብን የሚሰጥ (መዝ. 134
(135)፥25፤ ምሳ. 13፥23) ሀበነ ዮም ሲሳየነ
ዘለለ ዕለትነ። ጌታ ያስተማረው ጸሎት።
**ሲሳየ - ሲሳዬነህ**

252.**ሲሻው - ሲሻ - ሲሹ**
ሲፈልገው ፣ ሲመኘው ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

253.**ሲነጋ**
ማለዳ ሲኾን፣ ጀምበር ስትወጣ፣ ወፎች
ሲንጫጩ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢኾን ይገጥማል።

254.**ሲደልል - ደለለኝ**
ሲያታልል፣ ሲያምታታ፣ ሲያጭበረብር...።
ያባት ስም በዕውቀቱ ቢል ይገጥማል።

255.**ሳለአምላክ**
አምላክ ካለ ዘንድ፣ መመኪያ ካለ ...።
ያባት ስም ጌታነኽ ቢል ይገጥማል።
**ሳለጌታ - ሳለኹ - ሳለእግዜር**

256.**ሳላስብ - ሳልለው - ሳልልህ**
ድንገት፣ በቶሎ ፣ ሳልዘጋጅ ...።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።

257.**ሳሙኤል** (ዕብ)
በእግዚአብሔር የተሰማ ወይም እግዚአብ
ሔር ሰማኝ ማለት ነው። ፤ እናቱ ጡት
በጣለ ጊዜ እንደ ስእለቷ ለእግዚአብሔር
አቀረበችው፤ በቤተ መቅደስ አደገ። ነቢዩ
ሳሙኤል ንጉሡ ሳዖልንና ንጉሥ ዳዊትን
ቅብዐ መንግሥት ቀብቶ ያነገሠ የእግዚአ
ብሔር ነቢይ ነው። (1ኛ ሳሙ. 2፥3 ፤ የሐ.
. 3፥24 ፤ 13፥20)

258.**ሳምንህ**
ባንተ ላይ እምነቴን ስጥልብህ ።
ያባት ስም ሰጠኸኝ ቢል ይገጥማል።

259.**ሳረይ** (ጉራ) ደባለኝ ማለት ነው።

260.**ሳሳኹልህ - ሳሱ**
ሰሰትኩ ፣ ተንገበገብኩ ...።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።

261.**ሳበ**
ዘርን፤ ከዚያም ከዚህም ወሰደ፤ ጎተተ።
ያባት ስም ዘርይኹን ቢል ይገጥማል።
**ሳበልኝ - ሳበሸዋ - ሳበይፋት**

262.**ሴም** (ዕብ)
የኖኅ ታላቅ ልጅ (ዘፍ.5፥32 ፤6፥10)
የሴም ወንድሞች ያፌትና ካም ናቸው።

263.**ስለሺ**
ስለ ብዙዎች ...።
ያባት ስም ተሾመ ቢል ይገጥማል።
**ስለናት - ስለወንድም - ስለወገን**

264.**ስመኝ**
ስፈልግ ፣ ሲሻኝ ...።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
**ስመኝህ - ስንመኝህ - ስመኘው**

265.**ስሜ - ስሜነህ**
ዝናዬ ፣ መጠሪያዬ ።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።
**ስመጥሩ - ስሜወርቅ- ስማቸው** (2)

266. **ስምዖን** (ዕብ)
ሰማ ፣ የጸሎት ምላሽ ማለት ነው።
በቅዱስ መጽሐፍ ዘጠኝ ሰዎች ተጠርተው በታል (ዘፍ. 29፥33) ። በዐዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ሲወሰድ ትንቢቱ ሲፈጸም ለማየት ይጠብቅ የነበረ ስምዖን አረጋዊ ነው (ሉቃ. 2፥25)።

267. **ስብሐት** (ግእ)
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብ ። ትርጕም፤ በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድርም ፍቅሩ ለሰው ኾነ (ሉቃ. 2፥14)።

እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ። ትርጕም፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀኸ (መዝ. 8፥2)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
**ስቡሕ - ስባሔ - ስብሐቱ - ስብሐቴ**
**ስብሐት ለአብ** = በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጊዜ መልክአ ሥላሴን የደረሱ ሊቅ በዚህ ስም ይታወቁ ነበር ።
**ስብሐተ ጻድቃን** ክርስትና ስምን ተመልከት።

268. **ስናፍቅኸ**
ስፈልግህ በጉጉት ፣ በተስፋ ስጠብቅህ አገኘኹኸ ማለት ነው።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
**ስናፍቅ - ስናፍቀው**

269. **ስንታየሁ** (ስንትአየሁ)
ደስታ፣ መከራ፣ ድህነት፣ ሀብት ...።
ያባት ስም ደስታ ቢል ይገጥማል።
**ስንቱ - ስንታዬ - ስንቴ**

270. **ስንሻው - ስሻው**
ስንፈልገው ፣ ስንጠብቀው ።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።

271. **ስኂን** (ስሒን)
የሚሸት የጭስ እንጨት። ሉባንጃ፣ ጥሩ ሽታ ያለው ነጭ ዕጣን።
**ስኂን ማርያም** - ክርስትና ስም ተመልከቱ

272. **ስጦታ - ስጦታው**
ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ። የተሰጠ ...።
በበአልና በደስታ ጊዜ የሚሰጥ፤
እንዲሁ መሥዋዕትና ቍርባን ስጦታዎች ናቸው። በብዙ ይተረጐማል (ዘጸ. 28፥38)።

273. **ስፈልግ - ስፈልግኸ**
የጠፋን ፣ ተሰወረን ማግኘት።
ያባት ስም ዱባለ ቢል ይገጥማል።

274. **ሶምሶን** (ዕብ.)
እናቱ መከና ትኖር ነበረና በመልአክ ብሥራት ፀነሰችው፤ ልጁም ተወልዶ እስራኤላውያንን ከፍልስጥኤማውያን አዳነ። ከልጅነቱ ጀምሮ ናዝራዊ ጠጕሩ ያልተላጨ ነበር (መሳ. 13፥1)።

275. **ሶፎንያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር የጠበቀው ፤ የሰወረው ማለት ነው ። ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ፥ የተበተኑት ልጆቼ፥ ቁርባኔን ያመጡልኛል ብሎ ትንቢት ተናገረ (ትን. ሶፎ. 1፥4 ፤ 3፥10)።



## - ሸ -

276. **ሸለለ**
ግጥም ገጠመ ፣ ፎከረ፣ አቅራራ ማነው የሚደፍረኝ አለ ። በዘመናዊ ደግሞ አማረበት፣ ተገዘናና ...። ማለት ነው።
ያባት ስም ጀግናው ቢል ይገጥማል።

277. **ሸለመው**
ስጦታን ፣ ሀብትን ፣ ዋጋውን ሰጠው።
ያባት ስም አዱኛ ቢል ይገጥማል።
**ሸለመ - ሸለሙት - ሸለሙ**
**ሸልም - ሸልመው - ሸልማት**

278. **ሸንኮሩ - ሸንኮር**
ጣፋጭነትን፣ መውደድን ያመለክታል።
ያባት ስም ጸደቀ ቢል ይገጥማል።

279. **ሸዊት** (ትግ)
ሠዊት (ግእ) ስንዴ ማለት ነው።

280. **ሸዋ**
ማእከላዊው የኢትዮጵያ ግዛት ነው።
**ሸዋረግ - ሸዋለማ - ሸዋለም**
**ሸዋለፋ - ሸዋሉል - ሸዋመብራት**
**ሸዋመና - ሸዋማረ - ሸዋማናለ**
**ሸዋረታ - ሸዋመብራት - ሸዋምኒል**
**ሸዋረዳ - ሸዋብርሃን - ሸዋታጠቅ**
**ሸዋነህ - ሸዋነጋ - ሸዋናፈቁ**
**ሸዋንግዛው - ሸዋንቅጣው - ሸዋንዳኝ**
**ሸዋንታጠቅ - ሸዋንገረመው**
**ሸዋንጣሰው - ሸዋዓለም - ሸዋአመነ**
**ሸዋዘመድ - ሸዋዘውዴ - ሸዋይልፋ**
**ሸዋይርጋ - ሸዋይስማ - ሸዋደም**
**ሸዋደግ - ሸዋፀጋ - ሸዋፈራ**
**ሸዋፈራሁ - ሸዋብዛ - ሸዋፍራው**

281. **ሸጋ** (ኦሮ)
ያማረ መልካም ደስ የሚል ማለት ነው።
ያባት ስም ወንድሙ ቢል ይገጥማል።
**ሸጋና - ሸጉ - ሸጉየ - ሸጋወርቅ**
**ሸጋው - ሸጌር - ሸጌና - ሸጌናው**

282. **ሸፈነወርቅ - ሸፈና** (ኦሮ)
ደበቀ ፣ አላሳይ አለ ...።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

283. **ሹመት**
ማዕርግ፣ ደረጃ፣ ክፍ ማለት... ።
ያባት ስም ተገኝ ቢል ይገጥማል።
**ሹምበዛ - ሹሙ - ሹሜ - ሹም**
**ሹምሸር - ሹመቱ - ሹምየ/ዬ/**

284. **ሺመልስ** (ሸመልስ)
ጀግንነትን ያመለክታል፤ የጉበዝ ጉበዝ ማለት ነው ...።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ፊታውራሪ ሺመልስ ሀብቴ ናቸው። ላገር ነጻነት ከተዋደቁት ጀግኖች አንዱ ዐርበኛ ነበሩ።
**ሺፈራው - ሺመላሽ - ሺመርጊያ**
**ሺመክት - ሺመካች - ሺሰማ**
**ሺመብራት - ሺበላይ - ሺበሺ**
**ሺበቃው - ሺበዛ - ሺባባው - ሺብሩ**
**ሺፈራሁ - ሺኩራ - ሺወርቁ**

285. **ሻማ** (ዶር) ግዛው ማለት ነው።

286. **ሻረው**
ከሥልጣንህ አውርደው፤ ኃይሉን ቀንስ።
ያለፈውን ዘመን በዐዲስ ለውጠው፣ ተካ።
ያባት ስም አባትነህ ቢል ይገጥማል።

ሥላሴ እግች የሮማን ወርቅ ባለቤት
ደጃዝማች በየነ መርዕድ ይባሉ ነበር።
**በየነህ - በያን (ጉራ)- በያኔ - በየኑ**

371.**በዳሳ** (ኦሮ) ሽልማት ማለት ነው።

372.**በጊዜው**
ባወቅቱ፣ በዘመኑ፣ በሰዓቱ ...።
ለሁሉም ጊዜ አለው ፤ ለመወለድ፣ ለመ
ሞት፣ ለመትከል፣ ለመንቀል (መክ. 3፥2)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።

373.**በግርማ - በግርማው**
ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በግርማ መለኮት
ይመጣል (ማቴ. 25፥31)።
ያባት ስም ይታየው ቢል ይገጥማል።

374.**በጎሰው**
ጥሩ፣ ደግ ፣ መልካም ሰው ...።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ወደ
እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ ተንኮል
የሌለበት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ ።
(ዮሐ. 1፥48)
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

375.**በጸሎቴ - በጸሎት**
በልመናዬ፣ በስለቴ፣ በመማጸኔ ...።
እግዚአብሔር የልጆቹን ጸሎት በደስታ
ይሰማል። ጸሎት ብዙ ኀይል አለው
(1ጴጥ. 3፥12 ፤ ያዕ. 5፥17)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

376.**በጽሐ** (ግእ)
ቀረበ፣ ደረሰ፣ መጣ፣ ተዳረሰ ።
ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ።
ትርጉም፤ ቃላቸው እስከ ዓለም ዳርቻ
ደረሰ (መዝ. 18(19)፥3)።
ያባት ስም ሠናይ ቢል ይገጥማል።

377.**በጸጋው**
በቸርነቱ ፣ በምሕረቱ ፣ በበጎነቱ
እግዚአብሔር በጸጋው ደህንነትን ፈጽ
ሟል (ኤፌ. 2፥6 ፤ 2ጢሞ. 1፥9)።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።

378.**በፈቃዱ - በፍቃዱ**
በአሺባይነቱ፣ በችሮታው፣ በቸርነቱ ...።
ያባት ስም በየነ ቢል ይገጥማል ።

379.**በፍርዱ** -
ነገሩን በማስተዋል እውነትን ከሐሰት መለ
የት (ዘዳ. 25፥1 ፤ ምሳ. 1፥3 ፤ 2፥8)።
ያባት ስም መሠረት ቢል ይገጥማል።
**በፍርዴ - በፍርዳቸው**

380.**በፍቅሩ**
ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል ? መከራ
ወይስ ጭንቀት ፥ ወይስ ስደት ፥ ወይስ
ራብ ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥
ወይስ ሰይፍ (ሮሜ. 8፥31)።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።

381.**በዳኔ** (ኦሮ)
መምነሸነሽ የምሥራች ተደሰትን ማለት
ነው።

382.**በዳዳ** (ኦሮ) ሀብታሙ ማለት ነው።

383.**ቡሊ** (ኦሮ)
ያደረ መሬት ማለት ነው።

384.**ቡልቻ** (ኦሮ) - **ቡልቱ**
አስተዳዳሪ ፣ አባዳሪ ማለት ነው።



385.**ቡሩክ - ቡሩኬ** (ግእ)
የተባረከ ፣ የተመሰገነ ፤ ክቡር
ወይኩን ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር።
ትርጉም፤ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ
ይኹን (መዝ. 112፥1 ሲራ 45 ፤ ሉቃ. 1፥
42 ፤ ዘጸ.29፥21)።

386.**ቡካ** (ዶር) በለው ማለት ነው።

387.**ቡዙታ** (ጉራ)
ነገር ዐዋቂ ኹሉን ያጠቃለለ ማለት ነው፤

388.**ቢልልኝ – ቢለው**
ቢፈቅድልኝ፤ እግዚአብሔር ቢያድለኝ...።
ያባት ስም ክብረት ቢል ይገጥማል ።

389.**ቢምረው - ቢምሩ**
ይቅር ቢለው ፤ ቢታረቀው ...።
ያባት ስም መልአኩ፣ ዳኛቸው ቢል ይገ
ጥማል ።

390.**ቢሠውር**
ከክፉ ቀን፣ ከመቅሰፍት ዘመን ...።
ከመከራ ፤ ከችግር ።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

391.**ቢረሳው**
ቢተወው፣ ችላ ቢለው ...።
ከመቆየት ብዛት ባያስታውሰው ።
ያባት ስም ግሩም ቢል ይገጥማል።

392.**ቢረዳኝ – ቢረዳው**
በችግሬ ፣ በመከራዬ ቢደግፈኝ ...።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

393.**ቢረጋ**
በአንድ ቦታ ቢቀመጥ፥ ቢወሰን ...።
ያባት ስም ወሰኑ ቢል ይገጥማል።

394.**ቢራራ**
ቢያዝን ፣ ይቅር ቢል ...።
ያባት ስም ወንድሙ ቢል ይገጥማል።

395.**ቢራቱ** (ኦሮ) **ቢራ - ብራ**
ነጋ፣ ክረምት ዐለፈ በጋ መጣ (መፀው
ደረሰ) ዐማርኛ ዛሬ ብራ ኾነ ይባላል ።
ቀኑ ፀሐይ ኾነ ማለት ነው።

396.**ቢሰማኝ**
ልመናዬን፣ ጸሎቴን፣ ጥያቄዬን ...።
ያባት ስም ቁምነገር ቢል ይገጥማል።

397.**ቢሰነብት**
ቢኖር፤ የተወሰነ ጊዜ ቢቆይ ...።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።

398.**ቢሰጠኝ**
ሀብት፣ ጸጋ፣ ክብር ...።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

399.**ቢሻው**
ቢፈልገው፣ ቢፈቅደው ማለት ነው።

400.**ቢቂላ (ኦሮ) በቀላ**
ጸደቀ ማለት ነው። የአበበ ቢቂላ አባት
በዚህ ስም ይታወቃሉ።

401.**ቢተው - ቢተውልኝ**
ይቅር ቢል ፣ ባይነካ ፣
ያባት ስም ፋንታ ቢል ይገጥማል።

402.**ቢነጋ**
ፀሓይ ስትወጣ ፣ ወፎች ሲንጫጩ።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።
**ቢነጋፀሓይ**

ወ

ከእሳቱም ውስጥ ቅዱስ ገብርኤል ካዳና ቸው ወጣቶች አንዱ (ዳን.3፥16 ፤ ስን. ታኅሣ. ገጽ 392)።

703. **አዛውንት**
ትልቅ ሰው ፤ አስታራቂ ፣ ሽማግሌ...።
ያባት ስም ሺመልስ ቢል ይገጥማል።

704. **አዝመራ**
መከር ወይም ያጨዳ ወቅት (ማቴ. 13፥ 39፤ ሉቃ. 10፥2፤ ሩት 1፥22)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
**አዝመራዬ - አዝመራው**

705. **አዝማች – አዝምቴ - አዝምት**
በፊት በፊት ይዞ የሚጓዝ ፊታውራሪ ...።
ያባት ስም ተፈራ ቢል ይገጥማል።

706. **አዝዋኘ** (ጉራ)አማረ ማለት ነው

707. **አየኹ – አየኹብርሃን**
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።
**አየኹብዙ - አየኹኝ - አየኹዓለም**
**አይተነው - አየልኝ - አየነ**
**አየናቸው - አየነው - አይቼኽ**
**አይቼው - አይነቴ - አየው - አዩኽ**

708. **አያልቅበት**
አይፈጸምበት፣ አይቸግረው ...።
ያባት ስም ብሩ ቢል ይገጥማል።

709. **አያና** (ኦሮ)
ዕድለኛ ፤ መልአክ ማለት ነው።
**አያናው - አያንሳ - አያንቱ - አያኖ**

710. **አይሳነው - አይሳን**
ኹሉን ማድረግ፣ መጀመርና መፈጸም..።

711. **አይተንፍሱ**
ጠላቶች ዝም ይበሉ፤ ጥቂትም አይናገሩ ማለት ነው።

712. **አይችሉኽም - አይችሉም**
አይወዳደሩህም፣ ታሸንፋቸዋለህ ...።
ያባት ስም በዕውቀት ቢል ይገጥማል።

713. **አይካ** (ዶር) ያዘው ማለት ነው።

714. **አይደፈር**
የሚችለው የለም ...።
ያባት ስም ድንበሩ ቢል ይገጥማል።

715. **አይጠገብ**
ታይቶ፣ ተሰምቶ፣ ተበልቶ ተጠጥቶ ...።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

716. **አደላ - አደላህ**
ለራሱ፣ ለወገኑ፣ አዘነበለ ...።
ያባት ስም ወገኔ ቢል ይገጥማል።

717. **አደራጀው**
በሀብት፣ በገንዘብ፣ በእምነት እንዲያድግ እንዲቋቋመው አደረገው።
ያባት ስም ባያሌው ቢል ይገጥማል።

718. **አደፍርስ - አደፍርሰው**
አሸብር፣ አሸብረው ፤ ደባልቀው ፣ አቀ ላቅለው ...። ማለት ነው።
ያባት ስም ቢተው ቢል ይገጥማል።

719. **አዱኛ** (ኦሮ)
አደን ከሚለው ግስ የወጣ ነው።
ሀብት ንብረት ጌትነት፣ ክብር ፣ ልዕልና ማግኘት ማለት ነው።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።



720. **አዳም**
የመጀመሪያው ሰው የሚጠራበት።
የስሙ ትርጕም ቀይ፤ የቀይ ዳማ ከመረሬ ጭቃ የተገኘ ከመሬት የተፈጠረ ማለት ነው። ሰዎችን ኹሉ ያመለክታል። (ዘፍ. 1፥26 ፤ 2፥19 ፤ 3፥19) ።
**አዳምጤና - አዳሙ - አዳምሰገድ** (ዐፄ ቍቢል) - **አደም** (ዐረ)
**አደመ** (ግእ) **አማረ ማለት ነው።**

721. **አዳነ**
የማዳን ሥራ ከእግዚአብሔር ወይም ከሚወለደው ወይም ከሌላው ክፍል ስለተ ፈጸመ ይህ የስም ስያሜ ይሰጣል።
**አዳነኝ - አድነው - አዳና - አዳኜ**
**አድኑ - አድኅኖም** (ትግ)- **አድናቸው**

722. **አድርሴ** (ጉራ) **አድርስ**
አድርሳቸው ማለት ነው።

723. **አድማስ – አድማሱ**
ሰማይና ምድር የተገናኘ የሚመስለው የም ድር ዳር ፤ የምሥራቅ ጮራ ስትፈነጥቅ የሚታየው ወጋገን ማለት ነው።
ያባት ስም ወሰኔ ቢል ይገጥማል። **አድ ማሴ - ኣድያም ሰገድ** (ዐፄ ኢያሱ)

724. **አድኅልኝ**
ጤና ኾኖ በሰላም ካደገ ለማለት ...።

725. **እገሬ** (ግእ)
የተወለድኩበት፣ ቦታዬ፣ የምወደው ...።
ያባት ስም ይልማ ቢል ይገጥማል።
**አገር-ዓለም - አገርነኽ**
**አገር-አቀኑ - አገር**

726. **አገኘኹ - አገኘ - አገኙኽ**
በዚህ ስም ይታወቁ የነበሩት ሠዓሊና ገጣሚ አገኘሁ እንግዳ ነበሩ።

727. **አገዘ - አግዘው**
ከዕርዳታ ጋር የተገናኘ ስም ነው ።
ያባት ስም ቸሩ ቢል ይገጥማል።
**አገዘው - አግዜ - አግዛቸው**

728. **አግባው - አግባቸው**
ከተተው፣ ወደ መኸል ጨምረው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል

729. **አግናጤዎስ** (ግሪ)
የሐዋርያት ተከታይ የኾነ ሊቀ ጳጳስ ፤ በሕፃንነቱ ጌታ እግር ላይ ተቀምጦ የነበረ ነው ተብሎ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይታ ወቃል (ማቴ. 19፥14)።

730. **አግደው – አግዳቸው - አግዴ**
ከጠላት ጠብቃቸው አሰማራው ...።
ከልክሌ፣ ጠብቄ፣ ማለት ነው።
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በዐዲስ አበባ የከተማውን ዝበያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሥርዓትና ንግዱን ያስፋፉ፣ ለመንግሥት ቀረጥ እንዲገባ ያስደረጉ፤ ጉምሩክን የመ ሠረቱ ነጋድራስ አግደው ይባሉ ነበር።

731. **አጐናፍር**
አጐነ - አጐነፈረ ...።
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

732. **አጓጓኸኝ**
ምራቄን አስዋጥከኝ ...።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።

733. **አጥላው**
ጥላውን፣ ጥላኽን ጋርደው፣ ድባቡን ...።
ያባት ስም ድባቤ ቢል ይገጥማል።
**አጥላባቸው - አጥላዬ**

734. **አጥናፌ**
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ቢል ፤ ከዳር እስከ ዳር ማለት ይኾናል።
በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በአደዋ ዘመቻ ጊዜ የታወቁ ዐርበኛ ቢቶወደድ አጥናፌ ይባሉ ነበር ።
ያባት ስም አድማስ ቢል ይገጥማል።
**አጥናፍ ዓለም - አጥናፉ** (አጽናፉ)
**አጥናፍ ሰገድ** (ዐፄ ገላውዴዎስ)

735. **አጽብሐ** (ግእ)
ከኢትዮጵያ ነገሥታት በፍቅር የገዙ ወንድማማቾች **አብርሃና አጽብሐ** ይባሉ ነበር ። መታሰቢያቸው ጥቅምት አራት ቀን ይከበራል (ስን.ባር)። በዘመናቸው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ዘመን ነበር አብርሃ ቀድሞ ስለሞተ አጽብሐ ግዛቱን ይዞ ብቻውን ቀጠለ (340 ዓ. ም.)።

736. **አፀደ** (ዐማ)
አጨደ ማለት ነው። **አፀደ ወይን** የአትክልት ቦታ ።ዐጸደን ተመልከት።

737. **አፈራ** – **አፈራው**
ፍሬ ፣ ዘር ማግኘት፤ ተማሪን አፈራ ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

738. **አፈወርቅ – አፈወርቂ** (ትግ)
በዚህ ስም የሚጠራው የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዮሐንስ **አፈወርቅ** ነው። በስብከቱ ጣዕም የተነሣ ምእመናን ያወጡለት ስም ነው (ስን.ግን. 12 ገ. 207)።

739. **ኡርጋ** (ጉራ) - **ኡርጋሞ**
የተጠጋ ማለት ነው ።

740. **ኡርጌ (ኦሮ) - ኡርጌሳ**
ሽቶ ወይም ጥሩ የሚሸት ማለት ነው።

741. **ኢሳይያስ (ዕብ)**
እግዚአብሔር ደኅንነት ነው ማለት ነው። ከታላላቆች ነቢያት አንዱ ነው። በንጉሡ ዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝ፣ በሕዝቅያስ ዘመን ነበር።
ይህ ስም በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ነው (ኢሳ. 1፥1)።

742. **ኢብሳ** (ኦሮ) ብርሃን ማለት ነው።

743. **ኢብኑ-መለክ** (ዕብ. ግእ)
የንጉሥ ልጅ ማለት ነው።
ንግሥት ሳባ ማይበላ በሚባለው ቦታ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች ። ልጁም የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ ስለኾነ ። ኢብነመለክ አለችው ። **ኢብኑ-ሐኪምን ፣ ምኒልክን** ተመልከት።

744. **ኢቲሳ (ኦሮ)**
ከልካይ ማለት ነው። አቡነ ተክለሃይማኖት የተወለዱበት ቦታ ።

745. **ኢትዮጵያ - ኢትዮፒስ**
ኹለተኛው የኩሽ ስም ነው ። በግሪክ ኢትዮፕስ ይባላል።

746. **ኢካ** (ዶር) ዘለለ ማለት ነው።

747. **ኢዩኤል**
እግዚአብሔር አምላክ ነው ማለት ነው። ከነቢያት አንዱ ነው (ኢዩ.1፥1)።



748. **ኢያሱ** (ዕብ)
እግዚአብሔር አዳኝ መድኀኒት ነው። ከሙሴ ቀጥሎ ሕዝበ እስራኤልን ተስፋዋ አገር መርቶ ያደረሰ ነው (ዘጸ. 33፥11)።

749. **ኢያቄም** (ዕብ.)
እግዚአብሔር መሥርቷል (የእግዚአብሔር ገንዘብ) ማለት ነው። የቅድስት ድንግል ማርያም አባት እና ሌሎችም በዚህ ስም ተጠርተዋል (2ኛ ነገሥ. 23፥34–24፥6)።

750. **ኢዮስያስ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ይደግፋል ማለት ነው ። የይሁዳ ንጉሥ የንጉሥ አሞጽ ልጅ ነበር። የስምንት ዓመት ልጅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ 31 ዓመት በእስራኤል ነገሠ። ከዳዊት ቤት ከነበሩት መልካም ነገሥታት የመጨረሻው ነው (1ኛ ነገሥ. 13፥2)።

751. **ኢዮቤል** (ዕብ.)
በዓለ ሃምሳ ከሰባት ሱባኤ ወይም ከ 49 ዓመት በኋላ ዐምሳኛው ዓመት (ዘሌ. 25፥1)።

752. **ኢዮአታም** (ዕብ)
እግዚአብሔር ፍጹም ነው ማለት ነው። የጌዴዎን ታናሽ ልጅ (መሳ. 9፥5)። ኹለተኛው 12ኛ የይሁዳ ንጉሥ ነው (ኢሳ.1፥1)።

753. **ኢዮብ** (ዕብ)
ብዙ መከራ የደረሰበትና የታገሠ እግዚአብሔርን ያከበር ሰው ነው (ኢዮ.1፥1)።

754. **ኤልሳዕ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ደኅንነት ፤ መድኀን መድኀኒቴ ማለት ነው (1ኛ ነገሥ. 19፥16 ፤ 2ኛ ነገ. 3፥11)።

755. **ኤልኤዜር** (ዕብ.) (አላዛር)
እግዚአብሔር ረድኤት ነው ማለት ነው ። የአብርሃም ቤት መጋቢ፤ አብርሃም ለልጁ ለይሥሐቅ ሚስት እንዲያመጣለት ወደ መስጴጦምያ ላከው ። በጸሎት እግዚአብሔርን ለምኖ ርብቃን አገኘ (ዘፍ. 15፥2፤ 24፥1)።

756. **ኤልሳዕ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ደኅንነት ነው ማለት ነው። በኤልያስ እንደተጠራ ሥራውን ትቶ እየተከተለ ያገለግለው ነበር ። ኤልያስ በሰረገላ በተወሰደ ጊዜ አየው። የኤልያስም መንፈስ ዐረፈበት። (1ነገሥ. 19፥16 ፤ 2ነገሥ. 3፥11 ፤ 2፥1 ፤ 4 ፤ 5 ፤ 6)

757. **ኤልያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ኀያል ጉልበቴ ነው ፤ ያድነኛል (ዐቃቤ ሀገር) ማለት ነው። ኤልያስ በቅዱስ መጽሀፍ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ አል ። (ማቴ. 11፥14 ፤ ማር. 8፥28 )
ኹለተኛው የስሙ ትርጕም የወይራ ዘይት ማለት ነው (1ኛ. ነገሥ. 17፥1)።

758. **ኤልያቄም** (ዕብ)
እግዚአብሔር ያስነሣል ማለት ነው። (ኢሳ. 36፥3–22)። በዚህ ስም ብዙዎች ተጠርተዋል።

759. **ኤራ** (ዶር) ዘዴኛ ማለት ነው።

760. **ኤርምያስ** (ዕብ)
እግዚአብሔር ርኅራኄ አለው ከፍ ያደርጋል ማለት ነው ፤ ከታላላቆቹ ነቢያት አንዱ ነው ። ኹለተኛው መጽሐፉ ሰቆቃወ ኤርምያስ ነው (ኤር. 1፥1)።

790. **እንግዳ**
ዐዲስ ወይም ከሌላ ወገን የመጣ ...።
(ዕብ. 11፥13 ፤ 1ጴጥ. 2፥11)
ላገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ እንዲል።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
**እንግዳወርቅ - እንግዱ - እንግዳዬ**
**እንግዳሸት - እንግዳው**
**እንግዳአየሁ - እንግዳወሰን**

791. **እውነቱ - እውነት**
ስሕተት የሌለበት ትክክለኛ።
(ቲቶ. 1፥1 ፤ ሮሜ. 1፥19 ፤ ዮሐ. 1፥14)።
ያባት ስም ገነነ ቢል ይገጥማል።

792. **እዛና** (እይዛና)
በኢትዮጵያ ነግሦ የነበረው የነገሥታቱ
የአብርሃ እና የአጽብሐ አባት ነው። የግ
እዝ ፊደልን ቅርጽ አሻሽሎ እንደ ግሪኩ
ከግራ ወደ ቀኝ እንዲጻፍ አድርጓል።

793. **እያዩ - እያቸው**
እየተመለከቱ ...።
ያባት ስም ታረቀኝ ቢል ይገጥማል

794. **እጅግአየኹ**
የበለጠ ነገር፣ የተዋበ ነገር አየሁ ...።
ያባት ስም ብዙነህ ቢል ይገጥማል
**እጅግነኽ - እጅጌ - እጅጉ**
**እጅግሰማኹ - እጅግ**

795. **እጓለ** (ግእ) - **እጓለጽዮን**
ልጅ ማለት ነው። የጽዮን ልጅ
ደቂቀ እጓለ እመሕያው እስከ ማእዜኑ
ታከብዱ ልበክሙ ። ትርጉም ፤ እናንተ
የሰው ልጆች እስከ መቼ ድረስ ልባችኹን
ታከብዳላችሁ (መዝ. 4፥2 ፤ ዮሐ.1፥52)።

796. **አላና** (ኦሮ)
በላይነህ ማለት ነው።
**አላ - አላኔሳ - አላኖ- አላኒ - አሉማ**

797. **አብሳ** (ኦሮ)
ቻይ ትዕግሥት ማለት ነው።

798. **አቶሮ** (ዶር) ቀብራራ ማለት ነው።

## - ከ -

799. **ከሃሊ** (ግእ) **ከሃሉ**
ታጋሽ፣ ከሀለ ሲል ቻለ ታገሠ። የሚችል
ቻይ፤ ኀይለኛ ብርቱ ማለት ነው
(ሩት. 2 ፤ ሉቃ. 24፥9፤ ፊልጵ. 4፥12)።

800. **ከለላ**
መከታ ፣ ቅጥር ፣ መጋረጃ ፣ ከመከራ
ሸፋኝ ፣ አዳኝ ...።
ያባት ስም ፍቅሩ ቢል ይገጥማል።
**ከለለው - ከለለ - ከልል - ከለላዬ**

801. **ከለቻ** (ኦሮ)
በገዳ ሕግ ውስጥ የሚገኝ ሕግ ነው።

802. **ከልሳ** (ዶር) ጥጋቡ ማለት ነው።

803. **ከልካይ - ከልከል - ከልከለው**
አይቻልም አይኾንም ባይ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

804. **ከሠተ** (ግእ)
ግልጥ ኾኖ ታየ ፤ ገለጠ ማለት ነው ።
ወተከሥተ አዕይንቲሆሙ ወአእመርዎ።
ትርጉም፤ ዐይናቸው ተገለጠና ዐወቁት
(ሉቃ. 24፥31)።



805. **ከሣቴ ብርሃን** - **ከሣቴ** (ግእ)
ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያ ጳጳስ ኾነው ከመ
ጡ በኋላ ከሣቴ ብርሃን ተባሉ ። ይህም
ማለት በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ብርሃን
አየ እንደተባለው፤ ለኢትዮጵያውያን የወ
ንጌል ብርሃንን ስለአበሩ ነው።
(ማቴ. 4፥16 ፤ ኢሳ. 9፥2)።
**ፍሬምናጦስን እና ሰላማን** ተመልከት።

806. **ከበረ**
ተሾመ፣ ተሸለመ፣ ማዕርግ አገኘ።
ያባት ስም ሰሜ ቢል ይገጥማል ።

807. **ከበበ - ከበበው**
ዙሪያውን ያዘ ፤ ዙሪያውን አጠረ ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል ።

808. **ከበደ**
ከበረ ማለት ነው።
በሚዛን፣ በቍጥር እና በግርማ ሞገስ ፣
በሀብት የከበረ፤ የሚበልጥ ማለት ነው።
(ሳሙ. 14፥26፤ ሲራ. 22፥14፤ ኢዮ.6፥3)።
**ከበዱ - ከበደም**(ትግ)

809. **ከተማ – ከተማው**
የደመቀ፣ የብዙዎች መኖሪያ ...።
ያባት ስም ጋረደው ቢል ይገጥማል።

810. **ከፈኒ** (ግእ. ኦሮ)
ልብሴ ማለት ነው። **ከፈና - ከፈያ**

811. **ከፈለኝ**
ካሰኝ፣ ዋጋ ሰጠኝ፣ ተካልኝ ...።
ያባት ስም በላይ ቢል ይገጥማል።
**ከፍአርጋቸው - ከፍያሉ**
**ከፍያለው - ከፍይበሉ - ከፍያለ**

812. **ኩማ** (ኦሮ) ሺ ማለት ነው።
**ከመልቻ - ኩሜ - ኩምሳ - ኩመራ**

813. **ኩራባቸው**
ኮፍነን ፣ ጅንን በልባቸው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።
**ኩሩ - ኩራቱ - ኩራልኝ**
**ኩርይ - ኩራ - ኲራን** ተመልከት።

814. **ኩፋ** (ኦሮ) ወደቀ ማለት ነው።

815. **ኵሉ** (ግእ) ኹሉ ማለት ነው።
**ኵሉብርሃን**

816. **ኪሮስ** (ግሪ)
በዚህ ስም እመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም በሥዕሏ ተገልጻ ያነጋገረችው
ጸሎተኛ መነኩስ አባ ኪሮስ በመባል የሚ
ታወቁ ጻድቅ ናቸው (ስን. ሐም. 8 ገጽ. 5
35–541)።

817. **ኪሩቤል** (ዕብ.) **ኪሩብ**
መንበር ተሸካሚዎች መላእክት፤ ሰማያው
ያን ፍጥረቶች ናቸው። አዳም በኀጢአት
በወደቀ ጊዜ ወደ ዔዴን ገነት ለመመለስ
እንዳይችል መንገዱን ይጠብቁ ዘንድ እግ
ዚአብሔር ኪሩቤልን አኖረ (ዘፍ.3፥24)።

818. **ኪነጥበብ**
የልዩ ልዩ ተግባረ እድ የዜማ፣ የድርሰት፣
የዘፈንም ሙያና ሥራ ። ብዙ ሰው ይጠ
ራበታል (ዘጸ.20፥4 ፤ 35፥30)።
መዝሙር ዘማሪ **ድምፃዊ ዲያቆን ኪነጥ
በብ ወልደ ቂርቆስ** በዚ ስሙ ይታወቃል።

819. **ኪያ** (ኦሮ) የእኔ ማለት ነው።

820. **ኪዳን** (ግእ) **ኪዳኔ**
የተዋዋልኩት ቃሌ ማለት ነው።
ተካየደ ካለው የወጣ ነው። ተዋዋለ፣ ቃል ኪዳን ተጋባ፣ ተማማለ ማለት ነው።
(ዘዳ. 29፥1 ፤ ኤር. 31፥31 ፤ 32፥33)።
ኪዳነ ወልድ (ዮሐ. 8፥51)።
**ኪዳነ ማርያም** ክርስትና ስም።
**ኪዳኑ - ኪዳኔ - ኪዳኒ - ኪዳን**
**ኪዳነ ወልድ** (ክር)

821. **ካሳዬ**
በጠፋው ምትክ ተተካልኝ፣ ዋጋ ሰጠኝ...።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።
**ካህሱ - ካሳ - ካሱ - ካሰኝ**
**ካሰው - ካሳኹን - ካህሣዬ (ትግ)**
**ካህሣይ - ካሤ - ካሣይ**

822. **ካሌብ** (ዐብ)
የማይፈራ ደፋር ድል አድራጊ ማለት ነው ፤ (ከልብ)።
በቅዱስ መጽሐፍ ከሙሴ ሞት በኋላ ከኢያሱ ጋር ኾኖ ሕዝበ እስራኤልን መርቷል። እስራኤልን እንዲሰልሉ ከተላኩት ከዐሥራ ኹለቱ ሰዎች አንዱ ነበር (ዘኍ 13፥6 ፤ 14) ።
በኢትዮጵያ ታሪክም ዐፄ ካሌብ ስመ ጥር ንጉሥ ነበሩ (417 - 527 ዓ.ም.)።
የንጉሥነት ሥልጣናቸውን ለልጃቸው ለገብረ መስቀል ሰጥተው፤ ዘውዳቸውን ለኢየሩሳሌም ገዳም ልከው መነኑ (ስን. ግን. 18 ገጽ 311)።

823. **ኬር** (ጉራ)
ሰላም ይኹን ማለት ነው።

824. **ኬና** (ኦሮ) ስጦታ ማለት ነው።

825. **ክብሩ**
በሀብት መበልጸግ ከበሬታ ማግኘት ...።
ክብሩ ይስፋ፤ እግዚአብሔር ይመስገን።
ከፍተኛነትነት ፤ ሰው በንጽሕናው ፤ በማዕርጉ ክብር ያገኛል (ሮሜ. 13፥7)።
ያባት ስም **ታዬ** ቢል ይገጥማል።
**ክብረዓለም - ክብረአብ**
**ክብረማርያም - ክብረት**
**ክብረቅዱሳን - ክብሮም**
**ክብረሥላሴ - ክብር - ክብሬ**

826. **ክንዴ**
የኀይል ፤ የመመኪያ ምሳሌ ነው።
እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከግብጻውያን ባርነት አወጣቸዋለኹ ። ከተገዢነታቸውም አድናቸዋለኹ ። በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋቸዋለሁ (ዘጸ. 6፥6 ፤ ኢሳ. 51፥9፤ መዝ. 17፥34፤ ሕዝ. 30፥25)።
ያባት ስም **ላቀው** ቢል ይገጥማል።
**ክንዴኹን - ክንዳለም - ክንዱ**
**ክንዴነው - ክንዴሀፍትይ (ትግ)**
**ክንድይ - ክንድያ(ጉራ)**

827. **ከበበው**
ዙሪያውን ያዘው ...።
ያባት ስም **በለው** ቢል ይገጥማል።

828. **ክንፈ - ክንፉ**
እንደ እጅ በግራና በቀኝ ጐን የበቀለ።
ለክርስትና ስም ቅጽል ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም **መልአኩ** ቢል ይገጥማል።
**ክንፈርግብ - ክንፈብርሃን- ክንፈወርቅ**
**ክንፈ ገብርኤል** ክርስትና ስም።

829. **ከፈተው**
መንገዱን፣ በሩን፣ መግቢያውን ...።
ያባት ስም **በለው** ቢል ይገጥማል።



830. **ክፍሉ**
ቦታው፣ ደረጃው ...።
ያባት ስም **ዘርዐ ብሩክ** ቢል ይገጥማል።
**ከፈለው - ክፍሌ - ክፍላይ (ትግ)**
**ክፍለ ማርያም** ክርስትና ስም ።

831. **ኩራን**
ወንድ ልጅ አገኘን...። ተቆነን፣ ተጓደድን፣ ተኩፋነን ።
ያባት ስም **በዕድሉ** ቢል ይገጥማል።
**ኩራ - ኩሬ - ኩሩ**

832. **ኮርሜ** (ኦሮ)
ወንድ፥ ጎበዝ ማለት ነው።

833. **ኮርጆ** (ኦሮ)
መያዣ ከረጢት ወይም ሙዳይ ሳንቲም ጌጣጌጥ ማስቀመጫ (ኮሮጆ) ማለት ነው።

834. **ኮከቡ - ኮከበ**
ኮከብ ተሸላሚ ...።
የከዋክብት ብዛት የእግዚአብሔርን ልግስና ምልክት ነው። አብርሃም እንደ ከዋክብት ዘሩ ኢንዲበዛ ተስፋ ተሰጠው (ዘፍ. 15፥5 ፤ ኢዮ. 22፥12 ፤ መ. 146፥4)።
ያባት ስም **አበራ** ቢል ይገጥማል።

## - ኻ -

835. **ኻብቴ** (ዐማ) **ካብት** (ግእ)
ከበተ ተከበተ ካለው ግስ ካብት (ኻብት) ይወጣል።
ወሀበ ሰጠ ከሚለው ግስ ደግሞ ሀብት ይወጣል። ለዚህ ሀብት የሚለውን ተመልከት።
**ኻብትዬ - ኻብቱ - ኻበታሙ**
**ኻብትነት - ኻብትደግ - ኻብታገኘሁ**
**ኻብቶም - ኻፍታም - ኻብትይመር**
**ኻፍታኢ - ኻፍታይ(ትግ)**

836. **ኹሉምታየ** (ሁሉምታየ)
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል
**ኹሉምይፈር - ኹሉምሰው**
**ኹሉበላይ - ኹሉታዬ - ኹልጊዜ**
**ኹሉዓለም - ኹሉአንተን - ኹሌ**
**ኹሉወርቅ - ኹሉዐዲስ**
**ኹሉአገርኽ - ኹሉይመር**
**ኹሉይማር - ኹሉንአየሁ**

837. **ኹነኛው**
ኹኔታው፣ ሥራው፣ ተፈጥሮው፣ መልኩ ቁመናው እሱን የመሰለ ለማለት ...።
ያባት ስም **ተገኘ** ቢል ይገጥማል።
**ኹነኝ - ኹንልኝ - ኹንያለው**

838. **ኾነልኝ - ኾነኝ**
ወላጆች ያሰቡት ነገር ሲኾንላቸው የሚሰየም ስም ነው ።
ያባት ስም **መኩሪያ** ቢል ይገጥማል።

## - ወ -

839. **ወህምያ** (ጉራ) ክብር ማለት ነው።

840. **ወሃቤጸጋ** (ግእ)
ጸጋን የሰጠ (የሚሰጥ) ማለት ነው ።
ያባት ስም **ፍጹም** ቢል ይገጥማል።

841. **ወለላ - ወለላው**
የተጣራው የማር ሰፈፍ ማለት ነው።
ያባት ስም **ማሩ** ቢል ይገጥማል።

842. **ወሌ** (ግእ. ዐረ)
ወለየ ገባ ተመረጠ ማለት ነው።

ወ

ለቁም ነገር መረጠ ፣ ለየ ለሹመት።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ታናሽ ወንድም ወሌ ብጡል የራስ ጉግሳ ወሌ አባት ናቸው።

843. **ወልደ-ነጐድጓድ**
የነጐድጓድ ልጆች ማለት ነው ።
የዮሐንስና የያዕቆብ አባት ነጐድጓድ ይባል ነበር (ማር. 3፥17)።

844. **ወልዴ** (ግእ)
ወልድየ ከሚለው ። ልጄ ማለት ነው።
ለክርስትና ስም ቅጽል ነው።
**ወልዱ - ወልዳይ - ወልደየስ**
**ወልደ ኢየሱስ** ክርስትና ስም።

845. **ወማ** (ኦሮ) በረከት ማለት ነው።

846. **ወረሰ**
ትምህርት፣ ሀብት፣ ለልጅ፣ ለዘመድ፣ ለወዳጅ የሚተላለፍ ንብረት (ዘፍ. 15፥3)።
ያባት ስም በጎይሉ ቢል ይገጥማል።
**ወራሹ - ወራሽ - ወራሼ**

847. **ወረታው**
ውለታው ፤ የበጎ ሥራ ዋጋው ...።
ያባት ስም ያዛቸው ቢል ይገጥማል።
**ወረቱ - ወረቴ - ወሮታው**

848. **ወረደ** (ግእ)
ዝቅ አለ፤ ከላይ ወደታች መጣ ...።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

849. **ወርቁ**
የከበረ ማዕድን የክብር እና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው (ዘፍ. 2፥11 ፤ 13፥2 ፤ 24፥53 ፤ ማቴ. 25፥11 ማቴ 10፥9 ፤ መዝ. 119፥72)።
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።
**ወርቃለም - ወርቄ - ወርቃለማሁ**
**ወርቀበዙ - ወርቅበዛ - ወርቅሰው**
**ወርቅሸት - ወርቅሸዋ - ወርቅች**
**ወርቅነህ - ወርቅነው - ወርቃየሁ**
**ወርቃገኘሁ - ወርቅዬ - ወርቅያንጥፉ**
**ወርቅአፈራሁ**

850. **ወሰኑ**
አንዱ ደነገጉ ቢኾን ።
ኹለተኛው ድንበሩ ከለሉ ማለት ነው።
ያባት ስም አይደፈር ቢል ይገጥማል።
**ወሰነው - ወሰኔ - ወሰና**
**ወሰናቸው - ወሰን - ወሰንሰገድ**
**ወሰንየለህ - ወሰንየለው - ወሰንዬ**

851. **ወንዳፍራሽ**
ያባት ስም እንተኹን ቢል ይገጥማል።
**ወንዳለም - ወንዳለ - ወንዳንተ**
**ወንድዬ - ወንዳወቅ - ወንዳንተነኽ**
**ወንዳየኹ - ወንዳየን - ወንዳይ**
**ወንዳገኘሁ - ወንዳጥር - ወንዳፈራሁ**
**ወንዳቸው**

852. **ወንድሙ**
ያባትና የእናት ልጅ። ከዚህም ሌላ በሥጋና በመንፈስ ፤ በፍቅርና በመረዳዳት፣ በጓደኝነት ያለ ኹሉ ወንድም ይባላል።
በሥጋ፣ በአገር ፣ በነገድ፣ በቤተሰብ፣ በወዳጅነት፣ በሃይማኖት (ሮሜ. 1፥13)።
ያባት ስም አዘዘው ቢል ይገጥማል።
**ወንድማገኘሁ - ወንድማገኝ -**
**ወንድሜ - ወንድሜነኽ - ወንድም**
**ወንድምኹኔ - ወንድምተካ**



**ወንድምበሻ - ወንድምነኽ**
**ወንድማለም - ወንድምገዛኹ**
**ወንድምገዛው - ወንድምሸዋ**
**ወንድምኹን - ወንድምጌታ**
**ወንድምጋሻ - ወንድምሸት**

853. **ወንድወሰን (ወንዶሰን)**
ወንድ ድንበር መጨረሻ ማለት ነው።
ያባት ስም ተሻገር ቢል ይገጥማል።
**ወንድአፈረ - ወንድይፍራው**
**ወንድይራድ - ወንድሻው - ወንዳጥር**
**ወንድያለው ወንድዬ - ወንድይፍራው**

854. **ወዩማ (ኦሮ)**
ተሻለህ ማለት ነው ።
**ወዩሳ (ኦሮ)** ደኅንነት ማለት ነው።

855. **ወያ** (ኦሮ)
በጣሊያን ጊዜ በኦጋዴን በኩል ይዋጉ ከነበሩት ጀግኖች አንዱ ደጃዝማች በቀለ ወያ አብሴ፤ አባታቸው ወያ ይባሉ ነበር።

856. **ወይራው**
እንጨቱ ጥሩ የኾነ የተመረጠ ። ዘይቱ ለመድኃኒት ፣ ለቅብዐ ቅዱስ ፣ ለምግብ ይኾናል። በምሳሌነት ደግሞ የብልጽግና የሀብት ምልክት ነው
(ዘዳ. 24፥20 ፤ መዝ. 127፥3 ፤ ሮሜ. 11፥17)።
ያባት ስም ሙሉነ ቢል ይገጥማል።

857. **ወዳጄ**
የምወደው ፣ ወዳጄ ልቤ ...።
ያባት ስም አያልቅበት ቢል ይገጥማል።
**ወዳጁ - ወዳጄነኽ - ወዳጄነው**
**ወዳጅ - ወዳጅኹን - ወዳጆ**
**ወዳጅነው**

858. **ወገኔ - ወገኑ - ወገን**
ዘመዴ ፣ አለኝታዬ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

859. **ወጋየሁ**
በዚህ ስም ከሚጠሩት አንዱ፤ በኢትዮጵያ ሰማቸው ከሚጠራ የመድረክ ተዋንያን አንዱ ወጋየሁ ንጋቱ ነበር።
(1936 - 1982 ዓ.ም.)።

860. **ወግደረሰ**
ወግ ማለት ከአባት የተላለፈ ሥርዓት ፣ ደንብ፣ ከሕግ የተነሳ የሚደረግ ልማድ ነው (1ቆሮ.11፥2 ፤ ተሰ. 2፥15 ፤ 3፥6)።
**ወግኽ - ወግበላ - ወግበዛ**
**ወጋዬ - ወግደረሰን - ወጌ - ወጉ**
**ወግአገር**

861. **ውብነኽ**
አምራው ውብነኽ በመባል የታወቁ በጣሊያን ጊዜ ዐርበኛ መሪ ከነበሩት አንዱ ራስ ውብነኽ ተሰማ ናቸው።
**ውብሸት - ውባቸው - ውባለ**
**ውብዬ - ውባንተ - ውባለም**
**ውበቴ - ውብይሻው - ውቤ**
**ውቤነኽ**

862. **ዋለልኝ - ዋለ**
ውለታ ጣለብኝ፣ ረዳኝ፣ አብሮኝ ቆየ ...።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

863. **ዋሕድ** (ግእ)
አንድ ማለት ነው።
ያባት ስም አካሉ ቢል ይገጥማል።

864. **ዋሬ** (ኦሮ) ረፋድ ማለት ነው።

ያባት ስም ሚዛኑ ቢል ይገጥማል።
**ዐየላቸው - ዐያሌው - ዐያልነህ**
**ዐየለወርቅ - ዐየለው**

892. **ዐወቀ**
ተማረ፣ አጠና፣ ለመደ፣ ተረዳ፣ ለየ፣ .
ልብ አደረገ ማለት ነው።

893. **ዐይኑ-ኵሉ** (ግእ) (**የኹሉዐይን**)
ዐይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ።
ትርጕም ፤ የኹሉ ዐይን አንተን ተስፋ
ያደርጋል (መዝ. 144(145)፥15)።
ያባት ስም **አንተነህ** ቢል ይገጥማል።

894. **ዐይናለም**
ብርሃንን ማየትን እንዲሁም የሰውን ጠባ
ይንና ስሜት ይገልጣል (ዘዳ.7፥16፤ ኢሳ.
5፥15 ፤ ሕዝ. 14፥16)።
**ዐይናበባ - ዐይናቸው - ዐይኔ**
**ዐይንዋጋ - ዐይናማው**

895. **ዐደመ**
ሰውን ሰበሰበ ፤ በድብቅ በስውር ዶለተ
መከረ ነገር ቀጠረ ማለት ነው። **አደመ**
ቢል አማረ ማለት ነው። አዳምን ተመል
ከት።

896. **ዐደራ** (**ሐደራ**)
ጠብቀው፣ ኃላፊነትን፣ ታማኝ ኹነህ ተገኝ
ያባት ስም **ታከለ** ቢል ይገጥማል።
**ዐደራዬ - ዐደራው**

897. **ዐዲሱ** (**ሐዲሱ** (**ግእ**))
ታይቶ ያልታወቀ ፣ ከዚህ በፊት ያልተሰ
ማ፣ ያልታየ ፣ ያልተዳሰሰ፣ ያልተቀመሰ።
ያባት ስም **መስፍን** ቢል ይገጥማል።
**ዐደሱ - ዐደሰ - ዐዲሴ** (ኦሮ)

898. **ዐጅበው - ዐጅቡ - ዐጅቤ**
አድምቀው፣ ምሳሌ፦ ዐጀባ ኾኗል ደጅህ
በየት ልይህ፤ እንዳለች ዘፋኝ።

899. **ዐጸደ ወይን – ዐጸደ**
የተከበበ የአትክልት ቦታ ጓሮ ።
**ዐጸደ ወይን** አፍለስከ እምግብጽ። ትር
ጕም፤ ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣኽ
(መዝ. 79(80)፥8)።

900. **ዓለማየሁ - ዓለሜ - ዓለም**
ዐዲስ ሕይወት አየሁ ...።
ዓለምን እግዚአብሔር አስገኘው ።
ጠቅላላ ፍጥረት የዓለምን ሕዝብ ማለት
ይኾናል (ዮሐ.1፥10 ፤ 16፥21)።
በዚህ ስም የዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ **ዓለማየሁ**
**ቴዎድሮስ** በእንግሊዞች ተማርኮ የተወሰ
ደው በዚህ ስም ይጠራል።
**ዓለሙ - ዓለሙብርሃን - ዓለማት**
**ዓለማያ - ዓለማይ - ዓለምሰፋ**
**ዓለምሸዋ - ዓለምቀረ - ዓለምቀና**
**ዓለምተሰፋ- ዓለምቢሻው- ዓለምባንተ**
**ዓለምብርሃኑ- ዓለምበጁ - ዓለምተድላ**
**ዓለምታየ - ዓለምነኽ - ዓለምነው**
**ዓለምነጋ - ዓለምዳሩ - ዓለምዘውድ**
**ዓለምሠናይ - ዓለምሸት**
**ዓለም ሰገድ** (ዐፄ ፋሲል)

901. **ዕርቀሰላም**
ጠብ ባለበት መካከል ሰላም ሲኾን ዕርቅ
ይባላል። ከፈጣሪ ጋር መታረቅ ፤ የሚያስ
ታርቁም ብፁዐን ተብለዋል። (ማቴ. 5፥9
፤ ፊል. 4፥2 )።
ያባት ስም **ወረደ** ቢል ይገጥማል።
**ዕርቅዓለም - ዕርቀኢየሱስ - ዕርቁ**
**ዕርቅኹን - ዕርቅይኹን**



902. **ዕርገቱ - ዕርገተ**
ከታች ወደላይ መውጣት ማለት ነው።
**ዕርገተ-ቃል** ቢል ክርስትና ስም ይኾናል።
(የሐ. ሥራ. 1፥6 ፤ ሉቃ. 24፥50፤ ዕብ. 9፥11)።

903. **ዕንቍ**
የከበረ ከባሕር ውስጥ የሚገኝ ሰዳፍ የም
ትወልደው ድንጋይ (ማቴ. 13፥45 ፤ ራእ.
21፥21)።
ያባት ስም **ብርሃን** ቢል ይገጥማል
**ዕንቍአየህ - ዕንቋይ** (**ትግ**)
**ዕንቍአየሁ - ዕንቈባሕርይ** (**ግእ**)
**ዕንቈ ሥላሴ** ክርስትና ስም።

904. **ዕንባቆም** (ዕብ.)
ትንቢት ተናጋሪ ጠቢብ የልብን የሚያውቅ
ማለት ነው (ዕን. 1፥1)።

905. **ዕዝራ** (ዕብ.)
ረዳ (ረድኤል) ማለት ነው ።
500 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት በም
ርኮ በባቢሎን የእስራኤላውያን ሊቀ ካህ
ናት የነበረ እና ጸሐፊ የነበረ ነው
(ዕዝ. 7፥1-7 ፤ 11)።

906. **ዕድሉ**
ሀብት መጣ ፣ ሀብታም ኾነ ...።
ያባት ስም **አማረ** ቢል ይገጥማል ።
**ዕድላም - ዕድሌወርቅ - ዕድል**

907. **ዕድሜ - ዕድሜዓለም**
ዘመን ፣ ጊዜ ...።
ያባት ስም **ዘለቀ** ቢል ይገጥማል።

908. **ዕፁብ** (**ግእ**) **- ዕፁብድንቅ**
ድንቅ፣ የሚደንቅ ከቡድ ነገር ማለት ነው ።

## - ዘ -

909. **ዘለለው**
ተራመደው ፣ አለፈው ...።
ያባት ስም **ሙላቱ** ቢል ይገጥማል።

910. **ዘለላው**
ፍሬዎች ያሉበት የሚያምር ሐረግ።
የወይን ፍሬ በወይን ሐረግ ላይ ተነባብሮ
ተንዠርግጎ የሚታይ (ዘኍ. 13፥23)።
ያባት ስም **አማረ** ቢል ይገጥማል።

911. **ዘለቀ**
ተሻገረ ፣ አለፈ ...።
ያባት ስም **ትእዛዙ** ቢል ይገጥማል።

912. **ዘላለም** (**ዘለዓለም** (**ግእ**))
ኹልጊዜ ፍጻሜና ወሰን የሌለው ማለት
ነው (መዝ. 89፥2)። **ለወንድም ለሴትም**
**ጸታ ይኾናል ። ያባት ስም ፣ ለይኩን፣**
**ለገሠ፣ ባየህ፣ ሰንቁ፣ ሰመኝ፣ እውነት፣**
**ምገስ፣ መሐሪ፣ ክብረት፣ ተመስገን ቢል**
ከኹሉም የሚገጥም ስም ነው።

913. **ዘመልአክ** (ግእ)
የመልአክ ነህ ማለት ነው።
ያባት ስም **ክብሩ** ቢል ይገጥማል።
ክርስትና ስምን ተመልከት።

914. **ዘመረ - ዘመረወርቅ**
አመሰገነ ፣ አንጐራጐረ ...።
ያባት ስም **ያሬድ** ቢል ይገጥማል።

915. **ዘመነ**
ዘመነ (ግእ) (ዘበነ) ዘመናዊ ኾነ ፤ ዘመን
ቆጠረ ማለት ይኾናል።
ያባት ስም **ዮሐንስ** ቢል ይገጥማል።
**ዘመነሰላም - ዘመኑ - ዘመኔ - ዘመን**

916. **ዘመድ**
የቅርብ ዘመድን ወይም ጠቅላላ ወገንን ሊያመለክት ይችላል (ሉቃ. 14፥12 )።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
**ዘመደወርቅ - ዘመዳገኘሁ - ዘመድ**
**ዘመድኹን - ዘመድኩን** (ግእ)
**ዘመድአገኝ - ዘመዴ - ዘመዱ**
**ዘመዳለም**

917. **ዘማቹ – ዘማቼ**
ለጦር፣ ለትምህርት፣ ለሥራ ተጉዋዥ ...።
ያባት ስም ሠራዊት ቢል ይገጥማል።

918. **ዘረመጭት** (ጉራ)
ምርጥ ዘር ማለት ነው።

919. **ዘሩባቤል** (ዕብ)
የባቢሎን ዘር ማለት ነው (1ኛ ዜና. 3፥16፤ 16–19) ።

920. **ዘርዐ ያዕቆብ**
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ንጉሥ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው ። ኢትዮጵያን ሠላሳ አራት ዓመት አስተዳድረዋል። መጽሐፍ አዋቂና ፣ ለሃይማኖት ቀናኢ ነበሩ (1426- 1460) ።

921. **ዘር-ይኹን (ዘሪኹን) - ዘርኹን**
እስከ ብዙ ትውልድ የሚወለድ ልጅ ዘር ይባላል (ዘፍ. 3፥15 ፤ 38፥8፤ ማር. 4፥1)።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

922. **ዘርዓይ ድረስ**
በጣሊያን አሰረኛ ኾኖ በሮም የጣሊያን ቋንቋ አስተርጓሚ የነበረ ፤ የራስ ዐሉላን ጎራዴ ይዞ በይሁዳ አንበሳ ሐውልት ላይ ቆመው ስለኢትዮጵያ ነጻነት የተናገረ ጀግና ናቸው። በስሙም የመጀመሪያ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ ተሰይማ ነበር።
**ዘርዐሠናይ - ዘርዐማርያም - ዘረብዙ**
**ዘርዐብሩክ - ዘርዐዳዊት - ዘርአበዛ**
**ዘርዐብርሃን - ዘርዓይ - ዘሩ**
**ዘርዐጽዮን**

923. **ዘርጋ – ዘርጋልኝ - ዘርጋው**
እጅኽን፣ ልብስኽን፣ ጸጋኽን ...።
ያባት ስም ምሕረት ቢል ይገጥማል።

924. **ዘርፉ - ዘርፍነህ**
አባት እና እናትን መሳይነትን፣ ያሳያል።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል ።

925. **ዘበርጋ** (ጉራ) አሰፋ ማለት ነው።

926. **ዘበነ (ዘመነ)**
**ዘበናይ (ዘመናይ) - ዘበኑ (ዘመኑ)**
ኹለተኛው ትርጉም
**ዘበነ (ግእ)** ጀርባ ኾነ ። (ዘባን)
ምዕረ በዘባንኪ ወምዕረ በገቦኪ፤ ማርያም ብዙኃ በሐዚለ ሕፃን ደከምኪ።
ትርጕም ። አንዴ በጀርባሽ አንዴ በወገብሽ ፤ (ሰቆቃ. ድን ገጽ 51.)

927. **ዘበአማን** (ግእ)
እውነተኛ ...።
ያባት ስም መንግሥቱ ቢል ይገጥማል።

928. **ዘብርሃን** (ግእ)
የብርሃን ...።
ያባት ስም መላኩ ቢል ይገጥማል።
ክርስትና ስምን ተመልከት (ዮሐ. 8፥12)።



929. **ዘብዴዎስ** (ዕብ)
ስጦታ ፤ ስጦታዬ ማለት ነው።
የያዕቆብና የዮሐንስ አባት (ማር.1፥19 ፤ ማቴ. 27፥56)።

930. **ዘነበ – ዘነቡ**
ዝናብ የበረከት ምሳሌ ነው።
ያባት ስም ፍሬው ቢል ይገጥማል።

931. **ዘንባባው - ዘንባባዬ**
ብዙ ሕዝብ ጌታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌ ምእንደሚመጣ በሰሙ ጊዜ፥ የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡ (ዮሐ. 12፥13) የሰላም ምልክት ነው።
አበበ ፣ አፈራ ፣ ጸደቀ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።

932. **ዘንጊዘር** (ጉራ) መከታ ማለት ነው።

933. **ዘኘኒ** (ጉራ) መለሰ ማለት ነው።

934. **ዘአልቦ** (ግእ)
ምንም የሌለ ማለት ነው።
ያባት ስም ወሰን ቢል ይገጥማል።

935. **ዘካርያስ** (ዕብ.)
እግዚአብሔርን የሚያስበው፤ (ዝኩር እግዚአብሔር) ማለት ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ ከ20 በላይ የሚኾኑ ሰዎች ተጠርተውበታል (ሉቃ.11፥51)።

936. **ዘኬዎስ** (ግሪ)
ንጹሕ እግዚአብሔር ያነጻው ።
የቀረጥ ተቀባዮች አለቃ የነበረ ባለጠጋ ቁመቱ ዐጭር የነበረ ሰው ፤ ጌታ ኢየሱስም በቤቱ ተስተናገደ (ሉቃ. 19፥1)።

937. **ዘወትር**
የኹልጊዜ ጸሎቴ፣ ናፍቆቴ ...።
ያባት ስም ወዳጀነኽ ቢል ይገጥማል።

938. **ዘውዳገኘኹ**
ንጉሥ እና ንግሥት የሚቀዳጁት ከወርቅ ዐልማዝ እና ከዕንቍ ከከበረ ድንጋይ የሚሠራ የክብር አክሊል ነው (2ኛ ዜና. 23፥11 ፤ ሕዝ. .21፥26 ፤ አስ. 2፥17 ፤ ራእ. 19፥12)። **ዘውዳይ -**
**ዘውዳቸው - ዘውድ - ዘውዱ**
**ዘውድነህ - ዘውዴ - ዘውድዓለም**

939. **ዘውገ** (ግእ) **ዘውገ ማዕነቅ**
ኹለት ጥንድ ጣምራ ወገን አደረገ ።
(ሉቃ. 2፥24 ፤ ምሳ. 17፥10)
**ዘውግ - ዘውግነህ**

940. **ዘድንግል**
የድንግል ማለት ነው።
ያባት ስም ዱባለ ቢል ይገጥማል።

941. **ዘገነ – ዘገነወርቅ - ዘገነው**
በእጁ መዳፍ አፈሰ፣ ተረፈሰ ...።
ያባት ስም ወርቁ ቢል ይገጥማል።

942. **ዘገየ - ዘገዬ - ዘግያለው**
ወደኋላ ቀየ ...።
ያባት ስም ዋሴ ቢል ይገጥማል።

943. **ዘፈረ** (ግእ) **- ዘፈረወርቅ**
ዘርፍ፣ የልብስ ጫፍ፣ ዳርቻ፣ ቅጽል (ዘኍ.15፥38 ዘዳ. 22፥12፤ ማቴ. 23፥5)
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
ክርስትና ስምን ተመልከት (ዮሐ. 8፥12፤ 1)።
**ዘፈረ ብርሃን - ዘፈረ ማርያም**

944. **ዙርባቸው - ዙርቤ**
ፊትኽን መልበባቸው ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

945. **ዛፉ - ዛፌ**
ዋርካው፣ ታላቁ ፤ ቁመታሙ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።

946. **ዜና**
ወሬ ፣ ዐዲስ ነገር፣ የምሥራች ...።
ያባት ስም መዋዕል ቢል ይገጥማል።
**ዜናው - ዜናዊ - ዜናነህ**
**ዜና ሥላሴ** ክርስትና ስም።

947. **ዝምታ**
አለመናገር ...። ማዳመጥ ...።
ያባት ስም ተሻለ ቢል ይገጥማል።
**ዝምበላቸው - ዝምታወርቅ**

948. **ዝቅአርጋቸው (ዝቃርጋቸው)**
ወረድ አርጋቸው ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።
**ዝቅአርጌ (ዝቃርጌ)**

949. **ዝናዬ - ዝና**
የኔ ዝና፣ ስሜ ገናና ኹነ፣ ገነነ ...።
ያባት ስም ባልካቸው ቢል ይገጥማል።
**ዝናኽብዙ - ዝናኽ**

950. **ዝናቡ - ዝናቤ - ዝናብነኽ**
በረከቱ፣ ጥጋቡ መጣ ...።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።

951. **ዝግጁ**
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

## - ዠ -

952. **ዠቅ-አለ - (ዠቃለ)**
እንደ ፈሰሰ በሰቶ መጣ ። በቁሙ ተንዠ
ረቀቀ፣ ወረደ ...።
ያባት ስም ጸጋው ቢል ይገጥማል።

953. **ዠማ (ጀማ)**
ጀ እና ዠ ተወራራሾች ናቸው።
በሰሜን ሸዋ መንዝና ተጉለትን የሚለይ
እንዲኹ በወሎ አዋሳኝ የሚያልፍ ታላቅ
ወንዝ። **ጀማው - ጀማነኽ**

954. **ዠቡሬ** (ጉራ) ዐለፈ ማለት ነው።

## - የ -

955. **የሉልወርቅ**
ከባሕር የሚገኝ የከበረ ዕንቁ (ዘፍ. 2፥12)።
ሉል ንጉሥ ሲነግሥ በእጁ የሚጨብጠው።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

956. **የሐረግ (ያረግ)**
ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የዘር ሐረግ ...።
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።

957. **የሐሳብ (ያሳብ) — ያሳብወርቅ**
የምኞቴ ፍጻሜ ተሟላ ...።
ያባት ስም ሞላ፤ ተገኘ ቢል ይገጥማል።

958. **የሚያምረው — የሚያምር**
የሚናፈቀው፣ የሚወደደው ...።
ያባት ስም ተሰፉ ቢል ይገጥማል

959. **የማታ**
በስተመጨረሻ የተገኘ ...።



ያባት ስም ይመር ፣ መኩሪያ ፣ ተድላ
ቢል ይገጥማል።
**የማታው - የማታፀሓይ - የማታነህ**

960. **የማርሸት (የማር-እሸት)**
የማር ወለላ፤ በጥቅምት ወር የሚቆረጥ።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።
**የማር - የማርውሃ**

961. **የማነ (ማእ) የማን - የማነብርሃን**
ቀኝ ማለት ነው ።
የማናይ - በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ፈያታዊ
ዘየማን በመንግሥትኽ በመጣኽ ጊዜ ዐስ
በኝ ብሎ ጌታን የተማጸነ (ሉቃ. 23፥40)።

962. **የምሩ - የምር**
እምላክ ይኽን ልጅ የሰጠን የእውነቱ
ይኾን? ማለት ይኾናል።
ያባት ስም ነጋ ቢል ይገጥማል ።

963. **የምሥራች**
በግእዝ ብሥራት ማለት ነው።
ዐዲስ ዜና፣ ዐዲስ ወሬ ...።
ያባት ስም ተሰማ ፣ ዕጓለጽዮን ፣ ቢል
ይገጥማል።

964. **የምሻው**
ያለምኩት፣ የምፈልገው ተገኘ።
ያባት ስም ወሰኔ ቢል ይገጥማል።

965. **የምወደው**
ዓይኔን የጣልኩበት ደስ የሚያሰኘኝ ...።
ያባት ስም ተገኘ፣ ታረቀኝ ቢል ይገጥማል

966. **የራስወርቅ**
ከዘውድ፣ ከአክሊል ቀጥሎ የራስ ወርቅ
አለ ። ክብሬ ነህ ለማለት ነው።
ያባት ስም አበራ ቢል ይገጥማል።

967. **የሱነህ**
በጥያቄ፣ እሱን ትመስላለህ ...።
ያባት ስም ተወዳጅ ቢል ይገጥማል።

968. **የሺ — የሺጌታ - የሺጥላ**
የብዙዎች፣ ረዳት መከታ ነህ ...።
ያባት ስም መኩሪያ ቢል ይገጥማል።

969. **የሻሸወርቅ**
ነጭ በፍታ፣ ሥሥ ራስ ማሠሪያ ፣ ነጭ
ሻሽ፤ መሸፈኛ ማለት ነው (ዘጸ. 34፥4)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

970. **የቃልኪዳን - የቃልነኽ**
በእግዚአብሔር ስም የተማማልንበት ቃል
የተገባባንበት ፤ ምስክር፣ ማጽኛ ...።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

971. **የቁየሰው - የቁየ**
በሕይወት ያለ፣ የሰነበተ ደስታ አየ ...።
ያባት ስም አበበ ቢል ይገጥማል።

972. **የኔኹን**
የግሌ ፣ የብቻዬ ኹን ...።
ያባት ስም ዳኛው ቢል ይገጥማል።
**የኔሰው - የኔነኽ - የኔዓለም**
**የኔመብት - የኔመንግሥት - የኔማር**
**የኔነው - የኔአባት - የኔአካል**
**የኔዐዛኝ - የኔንአየሁ - የኔውብ**
**የኔገዳም - የኔፈንታ**

973. **የባሕርሸት (የባሕር-እሸት)**
ያባት ስም አይጠገብ ቢል ይገጥማል።

974. **የነገው**
የዛሬው አበባ የነገ ፍሬው ...።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።

1005. **ይልሃል - ይላላ**
ይነግርሃል፣ ጥበብ፣ ሥርዓት፣ ሃይማ
ኖት ...።
ያባት ስም **ዘወንጌል** ቢል ይገጥማል።

1006. **ይላቅ - ይልቃል**
ይብለጥ፣ ከፍ ከፍ ይበል ...።
የአባት ስም **ፍቅሬ** ቢል ይገጥማል።

1007. **ይልማ**
ይለምልም፣ ዘሩ አዝመራው ይብዛ ...።
በዚህ ስም ለኢትዮጵያውያን ዘፋኞች የዘ
ፈን ግጥም በመግጠም ድርሰት ይደርሱ
የነበሩት የኪነጥበብ ሰው ገጣሚ **ይልማ**
**ገብረ አብ** ይታወቁበታል። -
**ይልማሸዋ - ይልማወርቅ**

1008. **ይመር - ይመሩ**
ቆንጆ ይኹን፣ በሥራው፣ በዕውቀቱ፣ በች
ሎታው፣ በጠባዩ ...።
ያባት ስም **በጸጋው** ቢል ይገጥማል።

1009. **ይመስገን**
ለገሰኝ፣ አበረከተልኝ ጌታ፣ ፈጣሪ ...።
ያባት ስም **ሰጠኝ** ቢል ይገጥማል።

1010. **ይመኑ - ይመን**
በሃይማኖት፤ ሃቁን ይቀበሉ ...።
ያባት ስም **በእውነቱ** ቢል ይገጥማል።

1011. **ይማለደኝ - ይማልድ**
ያስታርቀኝ፣ ይርዳኝ፣ ይለምንልኝ ...።
ያባት ስም **መልአኩ** ቢል ይገጥማል።

1012. **ይማር - ይምረኝ**
ይቅር ይበለኝ፣ ምሕረት ይድርግልኝ ...።
ያባት ስም **በፈቃዱ** ቢል ይገጥማል።

1013. **ይምጡበዝና**
ወሬውን ሰምተው፣ ታላቅነቱን ተረድተው
ያባት ስም **ዓለምቀና** ቢል ይገጥማል።

1014. **ይርጋ**
ይረጋጋ ፣ መንዋወጡ፣ ሰላም ማጣቱ ...።
ያባት ስም **ዓለሙ** ቢል ይገጥማል።
**ይርጋወሰን - ይርጉ - ይረጋል**
**ይርጋልኝ - ይርጋው - ይርጋለም**
**ይርጋሸዋ**

1015. **ይርበብ**
ይዘርጋ፤ ጸጋው፣ ስጦታው ...።
ያባት ስም **ክንፉ** ቢል ይገጥማል።

1016. **ይርዳው**
ይደግፈው ...።
ያባት ስም **ጊልዮን** ቢል ይገጥማል።
**ይርዳቸው - ይርዳ**

1017. **ይስማ**
ይረዳው ፣ ይነገረው ፤ ወደ ዐዲስ
ዓለም መምጣትኽን ...።
ያባት ስም **ዳኛቸው** ቢል ይገጥማል።
**ይስማው - ይስማሸዋ**

1018. **ይሥሐቅ (ዕብ.)**
መደሰት ወይም ይሥቃል ማለት ነው በእር
ጅና ዘመን ልጅ እንዴት ይወለዳል ብላ
ሥቃ ነበርና በዚሁ ተጠራ
(ዘፍ. 17፥17 ፤ 18፥9)።

1019. **ይስገድ - ይስገዱ**
ያጎንብሱ፣ ይንበርከኩ፣ ማለት ነው።
ያባት ስም **ለአምላክ** ቢል ይገጥማል።



1020. **ይስፋልኝ - ይስፋሸዋ**
በዓለም ይዳረስ ...። ከጠባብ ወደ ሰፊ .።
ያባት ስም **ዝናዬ** ቢል ይገጥማል።

1021. **ይሳለሙ - ይሳለሙህ**
ይስገዱ፣ ያደግድጉ፣ ለክብርህ ...።
ያባት ስም **በላቸው** ቢል ይገጥማል።

1022. **ይቁም - ይቁምላቸው**
በሕይወት ይቆይ፣ ቀጥ ይበል ...።
ያባት ስም **ትንቢቱ** ቢል ይገጥማል።

1023. **ይቅርታ - ይቅርታው**
ይቅር ለእግዚአብሔር ፤ ከኹሉ ይበ
ልጣል ...።
ያባት ስም **በልአንተ** ቢል ይገጥማል።

1024. **ይቅደም**
መጀመሪያ ይኹን ...።
ያባት ስም **በዕውቀቱ** ቢል ይገጥማል።

1025. **ይበል - ይበልጣል**
ይናገር፣ ይወደዳል ፣ ይድገመው ...።
ያባት ስም **በሱፈቃድ** ቢል ይገጥማል።

1026. **ይበቃል**
በቃ ስጦታው ...።
ያባት ስም **በኀሰው** ቢል ይገጥማል።

1027. **ይበይን**
በዳኝነት ይመልከት ፤ ይታይ ...።
ያባት ስም **በፍርዱ** ቢል ይገጥማል።

1028. **ይባስ**
ይበልጥ ...። የተሻለ ...።
ያባት ስም **አሠጋኸኝ** ቢል ይገጥማል።

1029. **ይባቤ** (ግእ)
የበበ ካለው ግስ የወጣ ነው። እልል
አለ ፣ ዘፈነ ። እልልታ ማለት ነው።

1030. **ይቤ** (ግእ) አለ ማለት ነው
ያባት ስም **በቃሉ** ቢል ይገጥማል።

1031. **ይብለጥ**
በችሎታው፣ በዕውቀቱ፣ በሥራው...።
ያባት ስም **ምስጋና** ቢል ይገጥማል።

1032. **ይብዛወርቅ**
ይጨመር ...።
ያባት ስም **ምኞቴ** ቢል ይገጥማል።

1033. **ይብቃ**
ተጨማሪ አይኑር ...።
ያባት ስም **ሀብቴ** ቢል ይገጥማል።

1034. **ይነገር**
ለሰው ይወራ፣ ዜናው ይሰማ ...።
ያባት ስም **ታምራት** ቢል ይገጥማል
**ይነግሩታል - ይናገር - ይናገሩ**

1035. **ይታረቅ**
ሰላም ይኹን፣ ሥራ ይሠራ ...።
ያባት ስም **አገሬ** ቢል ይገጥማል።

1036. **ይታየው**
ግልጽ ኾኖ፣ በጥራት፣ በርቀት ...።
ያባት ስም **ፍኖተጽዮን** ቢል ይገጥማል።
**ይታያል - ይታይ - ይታዩ**
**ይታይህ - ይታጠቁ - ይታፈሩ**

1149. **ገመና**
የውስጥ ሚስጥር ... የግል ጉዳይ ...።
ያባት ስም እንተነህ ቢል ይገጥማል።

1150. **ገመቹ** (ኦሮ)
ደስታ ማለት ነው።
**ገመቺ - ገመችስ - ገመቺሳ**

1151. **ገመዳ** (ኦሮ)
ደስተኛ ማለት ነው። **ገመዲ - ገመዱ**

1152. **ገሞራው** (ግእ)
ገመረ ቻለ ያዘ ከሚለው ፤ ብርቱ ፣ ኃይለኛ ፣ ኀበዝ ፣ አደጋና መከራን ቻይ ማለት ነው።
**ገሞራው** ካሳ የጣሊያን ጦርነት ጊዜ በጀግንነት የታወቁ ዐርበኛ ነበሩ።
**ገሞራ** (ግእ) ቃሉ ሲጠብቅ ደግሞ የበሰለ ማለት ነው **ፍሬው ገሞራ**።

1153. **ገረመው**
ገረመ ካለው ግስ የወጣ አስፈራ፣ ተገረመ ደነቀው ማለት ነው።
**ገረመኝ - ገረመን - ገርሙት**
**ገረሙ - ገራሙ - ገርማሜ**

1154. **ገሥግሥ**
በማለዳ በቶሎ ድረስ ፤ ተጣድፈህ ኺድ ማለት ነው።

1155. **ገረሡ** (ኦሮ)
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ዐርበኛ **ደጃዝማች ገረሡ ዱኪ** ናቸው።
(1897 - 1958 ዓ.ም.) ።

1156. **ገሪማ** (ግእ)
ድንቁ፣ የሚደነቁ፣ ተአምር ያደረጉ ...።
ከዘጠኙ ቅዱሳን አንዱ ይሥሐቅ የሚባሉት ገሪማ ይባላሉ። የግብር ስም ነው።
የሚታሰቡት ሰኔ 17 ቀን ነው
**ግሩምነህ - ገረማየ - ገራኝ - ግሩም**

1157. **ገሩ - ገርየ - ገርባባው**
ደጉ፣ ሩኅሩኁ፣ ቸሩ ...።
ያባት ስም **አንዳርጋቸው** ቢል ይገጥማል።

1158. **ገሰሰ — ገሰሰው - ገስስ**
ዳሰሰ፣ ነካ፣ ዳበሰ፣ ማለት ነው።
ሌላው ትርጉም ፤ ገለበጠ ፍርድን ሻረ ይኾናል።
ያባት ስም **በኀይሉ** ቢል ይገጥማል።

1159. **ገበየኹ**
በዐደዋ ዘመቻ ከዐፄ ምኒልክ ታዋቂ የጦር አዛዥ የነበሩ *ፊታውራሪ* **ገበየሁ** አባ ጎራው ነበሩ ።
የዲዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው፤
ገበየሁ በሞቱ ግባና ቀድሰው።
ተብሎ ስለጀግንነታቸው ተገጥሞላቸዋል።
**ገበየኽ - ገበዩ - ገበያ - ገበያነኽ**
**ገበያው**

1160. **ገብሬ (ገብረ)**
**ልጇ** ፣ አገልጋዬ ...። ማለት ነው
የክርስትና ስም ቅጽል **ገብረ ማርያም** ቢል ገብሬ ተብሎ በማሳጠር ይጠራበታል ።
**ገብርዬ**
በዚህ ስም **የዐፄ ቴዎድሮስ** የጦር አለቃ *ፊታውራሪ* **ገብርዬ** በክርስትና ስማቸው ገብረ ሕይወት ከእንግሊዙ የጦር **ጀኔራል** ናፒየር ወታደሮች ጋራ ሲዋጉ ዐርብ የስቅለት ዕለት ማለፋቸው ይነገራል።
**ገብሩ - ገብራይ** (ትግ)
**ገብረ ማርያም** ክርስትና ስም።



1161. **ገነሜ**
ማለደ ማለት ነው።
በጋሞጎፋ ካምባ የቋራ ማርያምን ቤተክርስቲያን በ1912 ዓ.ም.የተከሉት ደጃዝማች ገነሜ የሚባሉ ናቸው። **ገነመ - ገነሞ**

1162. **ገነነ - ገናናው - ገነነው**
ዐየለ፣ በረታ፣ በጣም ከበረ፣ ታላቅ ኾነ ታዋቂ ኾነ ማለት ነው።... ።
ያባት ስም **ኀይሌ** ቢል ይገጥማል።

1163. **ገኑት** (ጉራ) ጻድቅ ማለት ነው።

1164. **ገና - ገናሽት**
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የሚከበርበት ዓመታዊ በአል ።
ያባት ስም **ልደቱ** ቢል ይገጥማል።

1165. **ገንዘቤ - ገንዘብ - ገንዘቡ**
ሀብቴ፣ ዋጋዬ፣ ብሬ ...።
ያባት ስም **ተካ**፣ ቢል ይገጥማል።

1166. **ገኘሽብተ** (ጉራ)
አስታራቂ፣ (ታረቀኝ ማለት ነው።

1167. **ገዛኸኝ**
ዋጋ አወጣህብኝ ...። ተቆጣጠርከኝ ...።
በሲድኒ (አውስትራሊያ ) በተደረገ የኦሊምፒክ ውድድር በማራቶን እሽቅድድም አንደኛ በመኾን ያገሩን ስም ያስጠራ ገዛሀኝ አበራ በዚህ ስሙ ይታወቃል ። የማራቶን ሽልማቱን ለእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ቤተ መዘክር ሰጥቶ ቱሪስት እየጐበኘው ነው። **ገዛኝ - ገዜ - ገዛኢ**
**ገዙ - ገዛ - ገዛኸን - ገዛነው**

1168. **ገደቡ — ገደበ - ገደብ**
አቆመ ፣ የቀን መጨረሻው ጊዜን ያመለከታል ...።
ያባት ስም **ተሰማ** ቢል ይገጥማል።

1169. **ገድሉ - ገድሌ**
ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ እጅ እግራቸውን ለሰንሰለት ዐይናቸውን ለፍላት ሰጥተው የፈጸሙት መንፈሳዊ ተጋድሎ። ጻድቃን በጸሎት መጋደላቸው ፤ መልካም ሥራ መሥራታቸው፤ ጾሙ፣ ጸሎቱ፣ ስግደቱ ኹሉ ገድል ይባላል ።
በክርስትና ስም **ገድለ ጊዮርጊስ** ይባላል።

1170. **ገዳ** (ኦሮ) የኦሮሞ ሕግ ነው።

1171. **ገዳመ**
የመነኰሳት ፣ የመነኰሳውያት መኖሪያ።
ያባት ስም **ሊባኖስ** ቢል ይገጥማል።
**ገዳሙ - ገዳሜ - ገዳምነህ**

1172. **ጉልቱ**
ርስት ፣ ቦታ ...።
ያባት ስም **ይበቃል** ቢል ይገጥማል።
**ጉልተሞ - ጉልተ - ጉልቲ - ጉልታ**

1173. **ጉርሙ** (ኦሮ)
ቅርንጫፍ ማለት ነው።
የአደአ ባላባት ማኛ አምራች ገበሬ የነበሩት ጉርሙ ጎበና ገዳ በዚህ ስም ተጠርተውበታል።

1174. **ጉዳ** (ኦሮ)
ጉዳ ታላቅ ወይም ትልቅ ማለት ነው።

1175. **ጉዲሳ** (ኦሮ) - **ጉደታ**
አደገ ማለት ነው።

1202. **ጎባ** (ዶር) ጎበዜ ማለት ነው።

1203. **ጎይቶም** (ትግ)
ጌታቸው ማለት ነው። **ጎይታ - ጎየታ**

1204. **ጎዳናው - ጎዳና**
መንገዱ፣ ቀጥ ያለው ረዥሙ መንገድ።
ያባት ስም ታደሰ ቢል ይገጥማል።

1205. **ጐረፈ - ጐርፍነህ - ጐርፉ**
በዝቶ መጣ ፣ ተሰብስቦ ደረሰ ...።
ያባት ስም ገበያው ቢል ይገጥማል።

1206. **ጐሥዓ** (ግእ)
አገሣ፣ ተናገረ ጐሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ።
ትርጉም ፤ ልቤ መልካም ነገርን አወጣ
(መዝ. 44(45)፥1)ቅዳ. ማር.)።

1207. **ጐባ**
ነገድ ...።
ያባት ስም ተዋሐዱ ቢል ይገጥማል።
**ጐባኙን - ጐባዬ - ጐባወርፈቅ**
**ጐባዬነህ**

1208. **ጐሸሜ**
ነካ አደረገ ፤ በክንድ ፣ በነገር ...።
ያባት ስም ክንዴ ቢል ይገጥማል።
**ጐሸመ - ጐሸመ**

1209. **ጐሹ - ጐሸየ**
የበሬ ዝርያ ፣ በሬ የሚመስል ተዋጊ እን
ስሳ ፤ በዱር የሚኖር ተወዳጅ፣ ኃይለኛ
የኾነ ነው።
በዚህ ስም አራት ዐይና ጐሹ የቤተ ክርስ
ቲያን ሊቅ ይጠሩበታል ።

1210. **ጐበዜ**
የኔ ጐበዝ ማለት ነው፤ ጠንካራ ኾነ ...።
ዐጼ ተክለ ጊዮርጊስ ዳግማዊ (1860 -1864
ዓ.ም) ከዐፄ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ከዐፄ
ዮሐንስ በፊት የነገሡ ናቸው ። ከንግሥና
ቸው በፊት ዋግ ሥዩም ጎበዜ ተብለው
ይጠሩ ነበር።
**ጐበዘ - ጐበዛየኹ - ገበዝእ**
**ጐበዘይ - ጐበዝ - ጐበዝ**

1211. **ጓንጕል** (ኦሮ)
ጌጤነህ እንደ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የዋግ ሹም የነበ
ሩት ጓንጕል ብሩ ናቸው። በዐደዋ ጦርነት
በዐፄ ምኒልክ ትእዛዝ ከጣሊያን ጋር ጦር
ነት ላይ ተሳትፈዋል ። ዋግ ሹም የሚባለ
ው ሥልጣን ከዛጔ መንግሥት ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣ ሥልጣን ነው።

## - ጠ -

1212. **ጠበቀው**
አጋጅ እረኛ ኾነው፤ አዳነው፤ ቆየው።
ፈጣሪ፣ ንጉሥ፣ አባት፣ እረኛ ...።
(ኤር. 23፥1 ፤ ሕዝ. 34፥2 ፤ ዳን. 4፥17)።
ያባት ስም ያገርሰው ቢል ይገጥማል።
**ጠብቃቸው - ጠብቄ**

1213. **ጠና**
ጠነከረ፣ በረታ ፤ ወይም ቆየ፣ ደጅ ጠና።
ያባት ስም ምንይከሰው ቢል ይገጥማል።
**ጠናጋሻው - ጠናወርቅ**

1214. **ጠንክር**
በርታ፣ ጐብዝ፣ ብርታት አግኝ (ኢዮ.6፥12)
ያባት ስም ጎብረት ቢል ይገጥማል።



1215. **ጠየቁ – ጠይቅ**
ተረዱ ፣ ዕወቁ ...።
ያባት ስም ዝና ቢል ይገጥማል።

1216. **ጢሞቴዎስ** (ግሪ)
እግዚአብሔርን አክባሪ፤ እንዲሁም ደግ
ሞ ዘአልቦቱ ጥሪት (ሀብት ያላካበተ)
ማለት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በልስጥራን
ያገኘው ወጣት ነው።
(የሐ. ሥራ 16፥1–3) ብዙ ሰው በዚህ ሲ
ጠራበት አይታይም። ሊቃነ ጳጳሳትግን ይ
ጠሩበታል።

1217. **ጢኖ** (ኦሮ)
ትንሽ ወይም ጥቂት ማለት ነው።
በዚህ ስም በዐፄ ሱስንዮስ ዘመን የኦሮ
ሞን ነገድ፣ የዐፄ ሱስንዮስን ታሪክ የጻፉ
**አዛዥ ጢኖ** ይታወቁበታል።

1218. **ጣፋ** (ኦሮ.)
በዚህ ስም የሚታወቀው የረዥም የሩጫ
ውድድር ተወዳዳሪው **ጣፋ** ባይሳ ነው ።
በዚህም ኢትዮጵያ አገሩን በዓለም አሳው
ቋል።

1219. **ጣሰው - ጣሳቸው - ጣሴ**
ገፋ ፣ ከፈለው፣ በንጥቆ ገባ ማለት ነው።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ የማይጨ
ው ዐርበኛ **ደጃዝማች ጣሰው ዋለሉ**
ናቸው (1894 - 1947 ዓ.ም.)።

1220. **ጣዕሙ** (ግእ)
መጣፈጡ...። ምግቡ ሽቶው ...።
ጠዐሙ ወታእምሩ ከመ ኄር እግዚአብ
ሔር። ትርጉም፤ እግዚአብሔር ቸር እን
ደ ኾነ ቅመሱ እዩም (መዝ. 33(34)፥7)።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
**ጣዕምያለው - ጣዕሞ - ጣዕመ**

1221. **ጣፈጠ**
ጣዕምን ሰጠ ማለት ነው።
ጣም ተገኘ፣ ስኳር፣ ጨው፣ ቅመም፤
የሚሸት ሽቶ፣ ዕጣን (ሉቃ. 8፥14)።
ያባት ስም ሸንኩሩ ቢል ይገጥማል።

1222. **ጤንነት**
ደኅንነት ማለት ነው።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
**ጤናነህ - ጤናው - ጤናኹን**

1223. **ጥላዬ**
የኔ ጥላ ማለት ነው።
የሰው፣ የዛፍ የፀሓይ ከለላ ።
**ጥላኹን** - በዚህ ስም ከሚታወቁት
አንዱ ድምፃዊው ጥላኹን ገሠሠ ነው።
**ጥላዬነህ - ጥላ - ጥላነህ**

1224. **ጥምቀቱ**
የጥምቀት አይነት ልዩ ልዩ ነው። በውሃ
እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፤ በስቃይ
መጠመቅ፣ መንጻት፣ መለወጥ (ማር. 1፥4)
ያባት ስም ዮርዳኖስ ቢል ይገጥማል።
**ጥምቀቴ - ጥምቀተ**

1225. **ጥሩነህ**
መልከ መልካም ነህ፣ ደግ ሰው ነህ ...።
ያባት ስም ምግባሩ ቢል ይገጥማል።
**ጥሩሰው - ጥሩማዕድ - ጥሩምንጭ**
**ጥሩቀለም - ጥሩብርሃን - ጥሩ**
**ጥሩዓለሜ - ጥሩአየሁ - ጥሩአየ**
**ጥሩዐይኔ - ጥሩወርቁ - ጥሩዘር**
**ጥሩገበያ - ጥሩፀሓይ**

1226. **ጥሪት**
ሀብት፣ ቀሪ ገንዘብ የሚቀመጥ ...።
ያባት ስም አስነ ቢል ይገጥማል።